# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

84ኛ ዓመት ቁጥር 038 ጥቅምት 8 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል::

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia




# የባሕር በር ጥያቄ ሁለንተናዊ ፋይዳዎች

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

**ዜና ትንታኔ**

ኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ እድገቷን ለማፋጠን በአደባባይ የማይነሳ የነበረውን የባሕር በር ጥያቄ ባለፉት አራት ዓመታት ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ እያነሳች ትገኛለች:: የባሕር በር እና የወደብ አስፈላጊነት እንደ ኢትዮጵያ ላለ ሰፊ የቆዳ ስፋትና ብዙ ሕዝብ ላላት ሀገር ቁልፍ ጥያቄ ነው::

በዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ወገኔ ማርቆስ (ዶ/ር)፣ የባሕር በር ከፍተኛ የወጪና ገቢ ንግድ ልውውጥ የሚካሄድበት ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ጋር የንግድ ትስስርን ለመፍጠር የሚያስችል ወሳኝ መተላለፊያ መንገድ መሆኑን ይናገራሉ:: ወገኔ (ዶ/ር) እንዳሉት፣ ከዚህ አንጻር የባሕር በር ያላቸው ሀገራት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ተጠቃሚዎች ናቸው:: የባሕር በር ያላቸው ሀገራት የባህር በር ከሌላቸው ሀገራት ይልቅ የምርቶቻቸው ዋጋ አነስተኛ ስለሚሆን ምርታቸው በዓለም ገበያ ተመራጭ ይሆንላቸዋል::

የባሕር በር ያላቸው ሀገራት በኢንዱስትሪ፣ በቱሪዝም እና በሌሎችም ዘርፎችም ያደጉ ይሆናሉ:: ከዚህም ባሻገር

የባሕር በር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “ህንጻዎች ሲገነቡ ጂኦሎጂካል ዳታን መሠረት አድርገው ሊሆን ይገባል”

\- ፍሬወለጋ ገለታ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የፊዚክስ መምህር

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- ህንጻዎች ሲገነቡ ጂኦሎጂካል ዳታን መሠረት አድርገው ሊሆን እንደሚገባ በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የፊዚክስ መምህሩ ፍሬወለጋ ገለታ ገለጹ:: የመሬት መንቀጥቀጥ ድጋሚ ሊከሰት ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ተመላክቷል::

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የፊዚክስ መምህሩ ፍሬወለጋ ገለታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ሰሞኑን በአዋሽ ፈንታሌ አካባቢ ያጋጠመው የመሬት መንቀጥቀጥ ንዝረት አዲስ አበባ ከተማ ድረስ የተሰማ ንዝረት ፈጥሯል :: ከዚህ አኳያም ትላልቅ ህንጻዎች በሚገነቡበት ወቅት ጂኦሎጂካል ዳታን መሠረት በማድረግ እንዲሁም የመሬት መንቀጥቀጥን መከላከል የሚያስችል አሠራርን ሊከተሉ ይገባል::

የመሬት መንቀጥቀጥ በአለቶች ግጭትና መላቀቅ፣ በእሳተ-ገሞራ፣ በኬሚካልና ኒውክሌር ፍንዳታ እንዲሁም በሰው ሰራሽ መንገድ ሊከሰት እንደሚችል ገልጸው፣ የመሬት መንቀጥቀጥ በቀጣይም ሊከሰት ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል::

የመሬት መንቀጥቀጥ በሚከሰትበት ወቅት

“ህንጻዎች ሲገነቡ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የቴሌኮም ዘርፉ የአክሲዮን ሽያጭና ጠቀሜታ

ጌትነት ተስፋማርያም

**ዜና ትንታኔ**

የኢትዮጵያ መንግሥት የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ላይ ሰፊ ሚና እንዲኖረው የሚረዱ የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፎችን አዘጋጅቷል። የማክሮ ኢኮኖሚውን ማሻሻያ ተከትሎ በቴሌኮምና የፋይናንስ ዘርፎች ላይ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች እንዲሳተፉ ስትራቴጂያዊ ርምጃዎች መውሰዱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መግለጻቸው ይታወሳል።

የካፒታል ገበያን በማቋቋም ኢኮኖሚውን ለማቀላጠፍና ኢንቨስተሮችን ለመሳብ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። የካፒታል ገበያው የአክሲዮን ሽያጭ ሥርዓቱን ማዘመን በርካቶችን ለኢንቨስትመንት የሚስብ መሆኑን የምጣኔ ሀብት ምሁራን ይገልጻሉ፡፡

ሰሞኑን የ130 ዓመት አንጋፋውን ተቋም የኢትዮ

የቴሌኮም ዘርፉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory



Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565

# ሥልጠናው የተመዘገቡ ስኬቶችን ለማስቀጠል የሃሳብና የተግባር አንድነት ለመገንባት የሚያስችል ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ለሕዝብ ተወካዮችና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት እየተሰጠ ያለው የአቅም ግንባታ ሥልጠና በኢትዮጵያ የተመዘገቡ ስኬቶችን ለማስቀጠል የሃሳብና የተግባር አንድነትን ለመገንባት የሚያስችል ነው ሲሉ አፈጉባኤ ታገሰ ጫፎ ተናገሩ፡፡

ለሕዝብ ተወካዮችና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት «የህልም ጉልበት ለእምርታዊ እድገት » በሚል መሪ ሃሳብ የአቅም ግንባታ ሥልጠና እየተሰጣቸው ነው፡፡ ሥልጠናውም ለአንድ ሳምንት እንደሚቆይ ተጠቅሷል፡፡

የሥልጠናው መርሃ ግብር ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ ታገሰ ጫፎ፤ ሥልጠናው በኢትዮጵያ የተመዘገቡ ስኬቶችን አጠናክሮ ለማስቀጠል የሃሳብና የተግባር አንድነትን ለመገንባት የሚያስችል ነው፡፡

ሥልጠናው ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ያለውን ሁለተናዊ ስኬት ይበልጥ አጠናክሮ ለማስቀጠልና በእድገት ጉዞ የሚገጥሙ ፈተናዎች ለመፍታት የሃሳብና የተግባር አንድነትን ለመገንባት የሚያስችል ነው ብለዋል

የአቅም ግንባታ ሥልጠናው በሀገሪቱ የተመዘገቡ ስኬቶችን ለማስቀጠል፤ የሚገጥሙ ተግዳሮቶችን ለመፍታት የሚያስችሉ ግብዓቶችን የያዘና ተጨማሪ ሃሳቦች ከሠልጣኞች ለመጨመር እንደሚረዳም ተናግረዋል፡፡

ሥልጠናው በአንድ የአስተሳሰብ መንፈስ በመሥራት የተገኘውን እድገት ለማስቀጠልና በሁሉም ዘርፍ ውጤት ለማስመዝገብ የሚረዳ መሆኑን



**አፈጉባኤ ታገሰ ጫፎ**

ጠቅመው፤ መወያየት፣ መመካከር፣ መነጋገርና መሠልጠን፣ የተወያዩበትን ሃሳብ ተግባራዊ ማድረግ የሀገርን እድገት ለማስቀጠል ይረዳል ብለዋል፡፡

የአቅም ግንባታ ሥልጠናው የሕዝብ ተወካዮችና የፌደሬሽን ምክር ቤት አባላትን ዓለም አቀፋዊ፣ ቀጣናዊና ሀገራዊ ጉዳዮችን አውቀው የሀገሪቱን ስኬት እንዲያስቀጥሉ የሚያግዝ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ተስፋየ በልጅጌ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የአቅም ግንባታ ሥልጠናው ኢትዮጵያ የደረሰችበትን ሁለተናዊ ስኬት ለማስቀጠልና በስኬቶቿ የሚገጥማትን ተግዳሮቶች ለመፍታት የሚያስችል አቅም ለመገንባት፤ የሃሳብና የተግባር አንድነት ለማምጣት የሚረዳ ነው፡፡

የሕዝብ ተወካይና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት ዓለም አቀፋዊ፣ ቀጣናዊና ሀገራዊ ጉዳዮችን እንዲያውቁ፤ የሀገርን ስኬት እንዲያስቀጥሉ ትልቅ አቅም የሚፈጥር ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የአመራርነት አቅም የመገንባት ሥራ ላለፉት አራት ዓመታት እየተሠራበት እንደሆነ አስታውሰው፤ አሁንም የሚሰጠው ሥልጠና ተጨማሪ አቅምን ለማጎልበት የሚያግዝ ነው ብለዋል፡፡

ሥልጠናው የሀገሪቱ ስኬቶች ምንድን ናቸው? ተግዳሮቶችስ? የሚለውን በመለየት ስኬቶችን ይበልጥ አጠናክሮ ለማስቀጠል፤ ፈተናዎችንም ፈትቶና ተሻግሮ የታሰበውን ብልፅግና እውን ለማድረግ ትልቅ ፋይዳ አለው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የሃሳብና የተግባር አንድነትን ለማጠናከር፤ በጋራ ግብ በጋራ በመቆም ስኬትን ለማስመዝገብ ሥልጠናው ትልቅ ጠቀሜታ አለው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

ሥልጠናው የህልም ጉልበት ለእምርታዊ እድገት፤ ትርክት ከታሪካዊ ስብራት ለሀገር እምርታ፤ የፖለቲካ፣ የምጣኔ ሀብት፤ የውጭ ግንኙነት፣ የደህንነትና ፀጥታ፣ ተቋማዊ፣ ሥነ-ምግባር፣ የአመራር እምርታዎችን የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮችን የያዘ መሆኑን ገልጸው፤ ሠልጣኞች ሥልጠናውን ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉና ስኬቶችን ለማስቀጠል ተግዳሮቶችን ለመፍታት የሚያስችል ተጨማሪ ግብዓት እንዲሰጡ መልእክት አስተላልፈዋል፡፡



**አቶ ዘማች ክፍሌ**

## በዞኑ 322 የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ዲላ፡- በጌዴኦ ዞን 322 የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት ላይ መዋላቸውን የዞኑ ትምህርት መምሪያ አስታወቀ።

የጌዴኦ ዞን ትምህርት መምሪያ ኃላፊ አቶ ዘማች ክፍሌ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በዞኑ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል በታችኛው የትምህርት እርከን ላይ ትኩረት ተደርጓል። በዚህም በኅብረተሰቡ ተሳትፎ በሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደረጃቸውን የጠበቁ የቅድመ አንደኛ መማሪያ ክፍሎችን ተገብተው ለአገልግሎት በቅተዋል።

በጌዴኦ ዞን ባለፉት ሁለት ዓመታት ለቅድመ አንደኛ ትምህርት በተሰጠው ትኩረት 322 የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ማድረግ ተችሏል ያሉት አቶ ዘማች፤ የተገነቡት ትምህርት ቤቶች የትምህርት ጥራት ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት እንደሚያግዙ ገልጸዋል።

አሁን ላይ በጌዴኦ ልማት ማህበር እና በግብረ ሰናይ ድርጅቶች ከአሥራ አራት በላይ ሞዴል የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እየተገነቡ መሆኑን የገለጹት አቶ ዘማች፤ እነዚህን እያሰፋን በሁሉም አካባቢ የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተደራሽ ከማድረግ አኳያ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

የቅድመ አንደኛ ትምህርት ቤቶችን በስፋት ተገንብተው አገልግሎት መስጠት ቢጀምሩም ውጤታማነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተግዳሮቶች መኖራቸውን ያነሱት አቶ ዘማች፤ የህፃናት መጫወቻዎች እና መሰል የቅድመ አንደኛ የትምህርትን ቁሳቁሶች እጥረት መኖሩን ገልጸዋል።

ማህበረሰቡም ልጁን ወደ ትምህርት ቤት ከመላክ ባለፈ ትምህርት ቤቱን ተንከባክቦ በመያዝ ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ አለበት ያሉት አቶ ዘማች፤ የትምህርት ዘርፉን የማሻሻል ሥራ ለመንግሥት ብቻ የሚተው ባለመሆኑ ሕዝቡን ያሳተፉ የተለያዩ ሥራዎች ተግባራዊ እየተደረጉ መሆኑን አመልክተዋል።

ትምህርት ቤቶችን ምቹና ሳቢ ለማድረግ በተጀመረው በትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ ላይ አበረታች አፈፃጸም መመዝገቡን ገልጸው፤ የትምህርት ቤቱ መገንባት የነዋሪዎችን የዘመናት ጥያቄ መልስ የሰጠ ነው። በተለይ ከትምህርት ቤቶቹ በዕውቀታቸው የተሻሉ ልጆች እንዲወጡ በትኩረት እንደሚሠራ ተናግረዋል።

# "የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻው ዲያስፖራው በኢንቨስትመንት እንዲሠማራ ማነቃቂያ ተፈጥሯል"

- ዲያስፖራዎች

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻው ዲያስፖራ በብዛት በኢንቨስትመንት እንዲሠማራ ማነቃቂያ መፍጠሩን የተለያዩ ዲያስፖራዎች ገለጹ፡፡

ከካሊፎርኒያ ሎሳንጀለስ የመጡት አቶ ኃይለኢየሱስ መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ውጭ ሀገር ለሚኖሩ የዲያስፖራ አባላት በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ተሠማርተው ሀገራቸውንና ራሳቸውን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ከፍተኛ ማነቃቂያ ፈጥሯል፡፡

የኢኮኖሚ ማሻሻው ውጭ ለሚኖረው ዲያስፖራ ወደ ኢንቨስትመንት እንዲገባ ከፍተኛ ማነቃቂያ ነው ያሉት አቶ ኃይለኢየሱስ፣ መንግሥት በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የሚያበረታታ የውጭ የምንዛሬ ተመን በገበያ እንዲወሰን የሚያስችል ማስተካከያ ተደርጓል ብለዋል፡፡

ማሻሻያውን ተከትሎም እሳቸው በሆቴል ኢንዱስትሪው ወደ ሥራ ለመግባት መዘጋጀታቸውን ጠቅሰው፣ የማክሮ ኢኮኖሚው ማሻሻያ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

ማሻሻያው የተወሰነ የኑሮ ውድነትን ሊፈጥር የሚችል መሆኑን ገልጸው፣ የውጭ ንግድን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሻሽልና ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ፣ ከሀገር በሚወጡ እቃዎች ላይ አቅርቦት ችግር እንዳይፈጠር ያደርጋል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ዲያስፖራውም ማሻሻያውን ተከትሎ ወደ እንቅስቃሴ እንዲገቡ የሚያስችል መሆኑን በመግለጽ፣ አባላቱ ወደ ሀገር ቤት የሚልከውን የውጭ ምንዛሬ ከፍ እንዲል የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል፡፡



**አቶ ኤሊያስ ከበደ**

በሌላ በኩል በአዲስ አበባ የተሠሩት የኮሪደር ልማት ሥራዎች የከተማዋን ገጽታ መቀየሩን የገለጹት አቶ ኃይለኢየሱስ፣ በሌሎች ዓለም ሀገራት ከተሞች ላይ የሚታዩ መንገዶች፣ መብራቶች፣ እግረኛ፣ የሳይክል መንገዶችን ጨምሮ የመዝናኛና የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች መሠራታቸውን ገልጸዋል፡፡

ከዱባይ የመጡት አቶ ኤሊያስ ከበደ በበኩላቸው፣ ማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻው ለዲያስፖራው አባላትን ወደ ኢንቨስትመንት ለማምጣት የሚያስችል ማበረታቻ ነው፡፡

በኢንቨስትመንት ዘርፎች ላይ ለመሳተፍ ማቀዳቸውን ጠቅሰው፣ መንግሥት በሚያስቀምጠው አሠራርና መመሪያ መሠረት በኢንቨስትመንት ለመሳተፍ



**አቶ ኃይለኢየሱስ መንግሥቱ**

መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ የተሠራው የኮሪደር ልማት ከተማዋን እንደስሟ አበባ ያደረገ መሆኑን በመግለጽ፣ ከተማዋን ለነዋሪዎችና ለእንግዶች ምቹ ለማድረግ የተሠሩ ሥራዎች አበረታች መሆናቸውንም ገልጸዋል፡፡

በቅርቡ ኢትዮጵያ ወደ ተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ ትግበራ መግባቷ የሚታወስ ሲሆን የማሻሻያው ዓላማም የውጭ ምንዛሪ መዛባትን ማስተካከል፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል፣ኢንቨስትመንትን ማበረታታት የሚሉት ይገኙበታል፡፡

# ኢትዮጵያ የጸጥታው ምክር ቤት አባል ከሆነች የአፍሪካውያንን ጥቅም የማስጠበቅ አቅሟ ከፍተኛ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የጸጥታው ምክር ቤት አባል ከሆነች በዓለም መድረክ የአፍሪካውያንን ጥቅም የማስጠበቅ አቅሟ ከፍተኛ መሆኑን በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ሙሉጌታ ደበበ (ዶ/ር) አስታወቁ::

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ሙሉጌታ ደበበ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅቱ እ.ኤ.አ በ1945 ሲቋቋም ብዙ ሀገራትን ያካተተ አልነበረም:: ኢትዮጵያን ጨምሮ ግብፅ፣ ላይቤሪያ እና ደቡብ አፍሪካ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሥራች ቢሆኑም በጸጥታው ምክር ቤት አባል የሆነ አንድም አፍሪካዊ ሀገር የለም:: ድርጅቱም ከግማሽ ምዕተ ዓመት በኋላም ሳይሻሻል ሲቋቋም በነበረበት አቋም ላይ ይገኛል ብለዋል::

እንደ ዶክተሩ ገለጻ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ድርጅቱ እንዲሻሻልና የአፍሪካ ሀገራትም የጸጥታው ምክር ቤት አባል እንዲሆኑ እየጠየቁ ነው:: ኢትዮጵያ በተለያዩ የዓለም መድረኮች ላይ ለአፍሪካ ሀገራት ድምጽ መሆኗን አሳይታለች:: በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮችም አፍሪካውያን በተመድ ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት እንዲኖራቸው ጥያቄ እያቀረበች ነው:: ኢትዮጵያ የጸጥታው ምክር ቤት አባል ከሆነች ካላት ተሞክሮ አንጻር ለአፍሪካውያን ድምጽ መሆንና ጥቅማቸውን ማስጠበቅ እንደምትችል ገልጸዋል::

ኢትዮጵያ ከዓድዋ ጦርነት ጀምሮ ገናና ነጻ ሀገር ናት ያሉት ዶክተር ሙሉጌታ፤ ወራሪዎችን በማሸነፍ ነጻነቷን ያስከበረች ብቸኛ አፍሪካዊት ሀገር ናት:: ኢኮኖሚዋ በሚፈለገው ልክ ባያድግም በዓለም መድረክ ከፍተኛ ተሰሚነትና ድምጽ አላት:: ከዚህ አኳያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት አባል ለመሆን አስፈላጊውን መስፈርት እንደምታሟላ ተናግረዋል::

በዓለም መድረክ የአፍሪካን ሀገራት ጥቅም ለማስጠበቅ በአፍሪካ ያላትን ተቀባይነት ማጠናከርና የምትከተለውን የገለልተኛ መርኋን ማጠናከር እንዳለባት አብራርተዋል::

ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ አባል ለመሆን በቂ ታሪክ አላት የሚሉት መምህሩ፤ ኢትዮጵያ ለአፍሪካውያን ለነጻነት የተመረጠች ቦታ ናት:: ለአፍሪካ ነጻነት ከፍተኛ ዋጋ ከፍላለች፤ አፍሪካውያንን በማስተባበርም የአፍሪካ ሕብረትን መሥርታለች:: በዚህም የአፍሪካ ሀገራት ኢትዮጵያን እንደ አዳኝ ይመለከቷታል ነው ያሉት::



ሙሉጌታ ደበበ (ዶ/ር)

በርግጥ የጥቅም ፍላት ያላት ግብጽ የኢትዮጵያ ገናናነት ለማኮሰስ ብዙ እንደምትሠራ ገልጸዋል:: አሁን ኢትዮጵያ ወደ ጥሩ መስመር እየገባች በመሆኑ በጸጥታው ምክር ቤት መሻሻል ላይ የምታነሳው ጥያቄ እውን ይሆናል:: የዓለም ሥርዓት መለወጥ አለበት፤ ለዚህም ኢትዮጵያ ጥያቄዋን በማቅረብ አጀንዳ ማድረግ ችላለች ብለዋል::

በሊግ ኦፍኔሽን፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በአፍሪካ ሕብረት ምስረታ ላይ ኢትዮጵያ ትልቅ ሚና ነበራት:: እንዲሁም በቅኝ አገዛዝ ውስጥ የነበሩ ሀገሮችን ነጻ ከማውጣት አንጻር በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላት አበርክቶ ከሃያላን ሀገራት ተርታ ያሰልፋታል:: ለዓለም ሰላም መስፈን ከማንኛውም ሀገር በላይ የጎላ ሚና እንዳላትም ገልጸዋል::

ተመድ አሠራሩን እንዲያሻሽልና አፍሪካም እንድትወከል የምታደርገውን ጥረት አጠናክራ መቀጠል እንዳለባት ዶክተር ሙሉጌታ ገልጸዋል::

# በመዲናዋ ከ180 ሺህ በላይ እናቶች በቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም ተጠቃሚ ሆነዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመዲዋ ከ180 ሺህ በላይ እናቶችን በቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም ተጠቃሚ ማድረግ እንደተቻለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ ዶክተር ዮሐንስ ጫላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የቀዳማይ ልጅነት እድገት ፕሮግራም ከፅንስ እስከ 6 ዓመት ያለውን የእድሜ ክልል የሚያካትት ነው። ይህ የእድሜ ክልል በኢትዮጵያ ትኩረት ያልተሠጠው ነገር ግን ለሰው ልጆች እድገት ዋና መሠረት ነው። ከዚህ አኳያም በመዲዋ ከ180 ሺህ በላይ እናቶችን በቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡

ፕሮግራሙ ከጽንስ እስከ 6 ዓመት የእድሜ ክልል ላሉት ህፃናት የአልሚ ምግብ መስጠት፣ የህፃናት ማቆያና የህፃናት መጫወቻ ሥፍራዎች ውብና ማራኪ በሆነ መንገድ በመስራት ህፃናቱ በአካባቢያቸው ባሉ ቦታዎች እንዲዝናኑና እንዲጫወቱ ያግዛቸዋል ብለዋል።

ሕፃናት ከተፀነሱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 6 ዓመት ድረስ አእምሯዊና አካላዊ ጤናቸውና እድገታቸው ተጠብቆ እንዲወለዱ፣ ተደስተው እንዲያድጉ፣ በአካላቸውና በአዕምሯቸው የዳበሩ ዜጋ እንዲሆኑ በተጀመረው ነፍሰ-ጡር እናቶች፣ አጥቢ እናቶችንና ሕፃናት የቀጥታ አልሚ ምግብ ድጋፍ ተጠቃሚ መሆን መጀመራቸውንም አውስተዋል፡፡

የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ልጆቻቸውን በአካል፣ በአዕምሮ እና በሥነ ልቦና የተሟላ ጤንነት እንዲኖራቸው ልዩ ትኩረት የሚሰጥበት ፕሮግራም ነው ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፤ ፕሮግራሙ ከተጀመረ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከ180 ሺህ በላይ እናቶችን ተደራሽ ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

ከተማ አስተዳደሩ ፕሮግራሙን መሠረት በማድረግ ከአምሥት ሺህ 300 በላይ የቤት ለቤት የወላጆችና ያሳዳጊዎች የምክር ሰጪ ባለሙያዎችን አስልጥኖ አስመርቋል። በዚህም ከ180 ሺህ በላይ እናቶችን ተደራሽ በማድረግ የእድገት ውስንነት የተገኘባቸውን ህፃናት መጠን ከ13 በመቶ ወደ 11 በመቶ ዝቅ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል።

ባለሙያዎቹ የእድገት ውስንነት ያለባቸውን ህፃናት የመለየት፣ የመከታተል እንዲሁም የበለጠ ምርመራና ህክምና የሚያስፈልግ ከሆነ ደግሞ ወደ ሆስፒታል የማስተላለፍ ኃላፊነት እንዳለባቸው ገልጸው፤ ይህንንም ቤት ለቤት በመዘዋወር እንደሚያከናውኑ ገልጸዋል።



ዶክተር ዮሐንስ ጫላ

የቀዳማይ ልጅነት እንክብካቤ በከተማዋ የታቀደውን ሥራ በስኬት ለመፈጸም የሚያስችል መሠረታዊ መንገድ ነው ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፤ ፕሮግራሙ የሕፃናትን ቤተሰቦች ተጠቃሚ የሚያደርግ፣ ወላጆች ልጆቻቸውን ተወዳዳሪ ዜጋ እንዲሆኑ የሚያስችል ፕሮግራም መሆኑን አስረድተዋል።

ከተማ አስተዳደሩ ፕሮግራሙ ከመጀመሩ በፊት በአዲስ አበባ ሕፃናት ለትምህርት ያላቸውን ዝግጁነትና አጠቃላይ የቀዳማይ ልጅነት እንክብካቤ ያለበትን ደረጃ በጥናት የፈተሸ ሲሆን በጥናቱ ግኝት መሠረት ዕድሜያቸው ከሦስት ዓመት በታች ካሉ ስምንት ሕፃናት አንዱ ወይም 13 በመቶ ያህል በዕድሜያቸው ሊደርሱበት ከሚገባቸው ዕድገት ደረጃ በታች መሆናቸው ተረጋግጧል ብለዋል።

ይህ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካለው አምስት በመቶ ከፍ ያለ ሲሆን የኢኮኖሚ ችግር ባለባቸው ቤተሰቦች ውስጥ የሚያድጉ ሕፃናት የተሻለ ቤተሰብ ውስጥ ከሚያድጉ እኩዮቻቸው የትምህርት ቅቡልነታቸው አነስተኛ መሆኑንም ይጠቁማል ነው ያሉት፡፡

እ.ኤ.አ. በ2026 በቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራም 330 ሺሕ እናቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

# ኢትዮጵያ ለቀጣናው ሰላም ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች ነው

**አዲሱ ገረመው**

ቢሾፍቱ፡- ኢትዮጵያ በቀጣናው ሰላምን ለማስከበር እየተጫወተች ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑ ተገለጸ:: በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ሲካሄድ የነበረው የአፍሪካ መከላከያ ሚኒስትሮች ጉባዔ ተጠናቀቀ::

የዩጋንዳ መከላከያ ሚኒስትር ጃኮብ አቦት ሰሞኑን በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት እየተካሄደ ባለው የአፍሪካ መከላከያ ሚኒስትሮች ጉባዔ ጎን ለጎን የኢፌዴሪ አየር ኃይልን በጎበኙበት ወቅት ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ የኢፌዴሪ አየር ኃይል ታሪኩና ያለበት ቁመና የሚደነቅ ነው ብለዋል:: ኢትዮጵያ በታሪክ በሰላም ማስከበር ሥራዎች ለቀጣናው ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከቷንም ገልጸዋል::

ኢትዮጵያ በሰላም ማስከበር ተልዕኮ ታሪካዊ ሚና ያላት ሀገር ናት ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህ እንቅስቃሴዋ ፓን አፍሪካኒዝምን እስከማምጣት የደረሰ መሆኑን ጠቅሰዋል::

ኢትዮጵያ የሌሎችን ሀገራት ችግርን እንደ ራሷ ችግር አድርጋ በመቀበል በእኔነት ስሜት ችግሮችን ለመፍታት በቁርጠኝነት የምትሰራ ሀገር መሆኗንም ሚኒስትሩ አስታውቀዋል:: ይህም በአፍሪካ በሰላም ማስከበር ሥራ ከፍተኛ ድርሻ ያበረከተች ሀገር አድርጓታል ነው ያሉት::

ዩጋንዳ ከኢትዮጵያ ጋር የረጅም ጊዜ ወታደራዊ ግንኙነት ያላት ሀገር ናት በማለት፤ በተለይም በሥልጠና፣ በደህንነትና ሌሎች መስኮች ላይ በጋራ እንደምትሠራም ገልጸዋል::



የአፍሪካ መከላከያ ሚኒስትሮች ጉባኤ"አፍሪካ በጠንካራ አንድነት፣ ለሁለንተናዊ ፀጥታና ሰላም" በሚል መሪ ሃሳብ በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ሲካሄድ የነበረው ጉባዔ የተጠናቀቀ ሲሆን፤ የጉባዔው ተሳታፊዎች የአፍሪካ ሀገራት መከላከያ ሚኒስትሮች እና ወታደራዊ አታሼዎች ቢሾፍቱ የሚገኘውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ አየር ኃይል በመገኘት የሥልጠና እና የጥገና ማእከላትን እንዲሁም የበረራ ትምህርት ቤትን ጎብኝተዋል:: ከዚህም ባሻገር በትናትናው ዕለትም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደርንና ሌሎች ተቋማትን ጎብኝተዋል::

የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሀመድ በተለይም ትናንት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደርንና የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩትን በተጎበኘበት ወቅት እንደገለጹት፤ ተቋማቱ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም መሥራት እንደሚችሉ ተናግረዋል። ሁለቱ ተቋማት ያላቸውን ልምድና እውቀት ማከፈላቸውም የዚሁ ማሳያ እንደሆነ አንስተዋል።

እንደ አህጉር ችግሮችን ለመፍታትም በጋራ መቆም ይገባናል በማለት፤ እንዲህ አይነት ተቋማትን መመስረት የሚፈልጉ ሀገራትን ለማገዝ ኢትዮጵያ ዝግጁ መሆኗንም ገልጸዋል::

ተሳታፊዎች በጉብኝታቸው ወቅት፤ ኢትዮጵያ በሰላም ማስከበር ሥራ ላይ ብቻ ሳትሆን ለሌሎች ሀገራት ጭምር በማሠልጠን ለቀጣናው ሰላምና መረጋጋት ትልቅ ሚናን እየተጫወተች እንዳለ ገልጸዋል:: ይህ የመሪነት ሚና የአፍሪካ ሀገራትን የጋራ ደህንነት አቅም ለማጠናከር ወሳኝ መሆኑንም ነው ያመላከቱት:: ኢትዮጵያ ለቀጣናው ሰላም እያበረከተች ካለው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ባሻገር የደህንነት ተቋማቶቿ ለሌሎችም አስተማሪ መሆናቸውን ገልጸዋል::

ጉባዔው የአፍሪካ ህብረትን "አፍሪካዊ ለአፍሪካ ችግሮች መፍትሄ" የሚለውን መርህ በማንፀባረቅ በሰላም ማስከበር ተልእኮዎች ውስጥ አንድነትን እና በራስ መተማመንን የማጎልበት ሰፊ የአፍሪካ አጀንዳን ያረጋግጣል የተባለ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ለሰላም ማስከበር የምታበረክተው አስተዋፅኦ ለዚህ ራዕይ ወሳኝ ሆኖ በመታየት ሀገሪቷን በአህጉሪቱ ዘላቂ ሰላም በማስፈን ረገድ ቁልፍ ተዋናይ አድርጓታል ሲሉ የጉባዔው ተሳታፊዎች ምስክርነት ሰጥተዋል።

# በከተማዋ ከ690 ሺህ በላይ ህጻናት የፖሊዮ ክትባት ተሠጥቷል

**ማህሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደው የልጅነት ልምሻ ወይም የፖሊዮ ክትባት በዘመቻ ከ690 ሺህ በላይ ህጻናት የፖሊዮ ክትባት መስጠት መቻሉን ከተማው አስተዳደር ጤና ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የህብረተሰብ ጤና ምርምር እና ድንገተኛ አደጋዎች ቁጥጥር ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ዳምጠው ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የልጅነት ልምሻ ወይም የፖሊዮ ቫይረስ በተበከለ ምግብና ውሃ አማካኝት የሚመጣ ሲሆን ሕፃናትን ለዘላቂ አካል ጉዳት ብሎም ለሞት የሚዳርግ አደገኛ በሽታ ነው፡፡

ይህንን ለመከላከልም እንደከተማ ከመስከረም 27 ቀን 2017 ዓ.ም እስከ ጥቅምት 02 ቀን 2017 ዓ.ም ለስድስት ቀናት የልጅነት ልምሻ ወይም የፖሊዮ ክትባት ዘመቻ የተካሄደ መሆኑን ገልጸው፤ በዘመቻውም ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ 628 ሺህ 714 ህጻናት ለመከተብ ታቅዶ 691 ሺህ 206 ያህል ህጻናት ክትባት መስጠት መቻሉን አስታውቀዋል፡፡

የክትባት ዘመቻው ቤት ለቤት ጨምሮ በትምህርት ቤት፣ በሕጻናት ማቆያ፣ በማሳደጊያ እና በሌሎች ሕጻናት በሚገኙባቸው ቦታዎች ሁሉ የተሰጠ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በዘመቻው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሁሉንም ህጻናት ከመከተብ በተጨማሪ ክትባት ያልጀመሩ ወይም ያቋረጡ ካሉ ወደ መደበኛ ሥርዓት ውስጥ የማስገባት እና ፖሊዮ መሰል ምልክቶች የሚታዩባቸው ህጻናቶች ካሉ የመለየት እቅድ በመያዝ የተካሄደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በዚህም በተደረገ አሰሳ 412 ክትባት ያልጀመሩ ወይም ያቋረጡ በጎዳና እና በማቆያ የሚገኙ ህጻናት መደበኛ ክትባትን እንዲጀምሩ ማድረግ የተቻለ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ቤት ለቤት በተደረገ አሰሳም ምንም አይነት በፖሊዮ የተጠቃ ወይም የሚያጠራጥር ህጻን አለመኖሩን ማየት የተቻለ ሲሆን ይህም መደበኛ የክትባት ፕሮግራም ምን ያህል አዋጭ መሆኑን የታየበት ነው ብለዋል፡፡

አቶ ዳንኤል እንደገለጹት፤ ክትባቱ ወረርሽን ከመከሰቱ በፊት የመከላከል አቅምን ለማሳደግ ይረዳል፡ ፡95 በመቶ ህጻናቶች የክትባት አገልግሎትን ካገኙ የከተማው የመከላከል አቅም ከፍተኛ የሚባል ሲሆን ከታቀደው በላይ ማሳካት በመቻሉም በከተማው ወረርሽኝ ቢከሰት እንኳን ህጻናቱ እንዳይጠቁ ለማድረግ ያስችላል፡፡

የፖሊዮ በሽታ በዋናነት ህጻናትን የሚያጠቃ በፖሊዮ ቫይረስ አማካኝነት የሚከሰት የእግር፣ የእጅ እንዲሁም የውጭ ክፍልን የሚያልፈሰፍስ በሽታ ሲሆን የሚተላለፍ መንገዱም በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር ባለ ንክኪ፣ በተበከለ ምግብ እና በተበከለ ውሃ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

በመሆኑም ንጽህናን ከመጠበቅ ባለፈ በዋነኝነት ክትባቱን በአግባቡ በመውሰድ ህጻናት ከበሽታ የመከላከል አቅማቸውን በማሳደግ የፖሊዮ በሽታን መከላከል ይገባል ብለዋል፡፡

በከተማዋ ለሚገኙ ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ሕጻናት በሙሉ ክትባት በመስጠት ወረርሽኝ እንዳይከሰት ለማድረግ የተካሄደው የክትባት ዘመቻ በሀገር አቀፍ ደረጃ የፖሊዮ ቫይረስን ለመከላከል የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት የሚያስችል መሆኑንም አንስተዋል፡፡

# የቴሌኮም ዘርፉ የአክሲዮን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ቴሌኮምን 10 በመቶ ድርሻ ለኢትዮጵያውያን ለመሸጥ መወሰኑን ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይፋ አድርገዋል። በቀጣይ ሰፊ የካፒታል ገበያ እንዳለ አመላክተው፤ ለአሁኑ ግን የኢትዮ ቴሌኮምን አክሲዮን በመግዛት ኢትዮጵያውያን ሊረባረቡ እንደሚገባ ነው ያሳሰቡት።

የኢትዮ ቴሌኮም ድርሻ ለመግዛትም ከዝቅተኛው ብር 9 ሺህ 900 ወይም 33 አክሲዮኖች ጀምሮ እስከ ከፍተኛው ብር 999 ሺህ 900 ወይም 3 ሺህ 333 አክሲዮኖች ድረስ መግዛት እንደሚቻልም ይፋ ተደርጓል። በኮሙኒኬሽን ዘርፍ የተጀመረው ለሻጩም ሆነ ለገዥው የሚያበረክተው ፋይዳ ምንድነው በሚሉ ጉዳዮች ላይ የዘርፉ አካላት ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ብሩክ ታዬ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ የኢትዮ ቴሌኮምን አክሲዮን ለመሸጥ የሚያስችሉ ዝግጅቶች በጥንቃቄ ተከናውነዋል፤ ሒደቱንም ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ያሟላና በእንግሊዝና ኬንያ የሚገኙ ተመሳሳይ ሥራ የሚያከናውኑ ተቋማት ጭምር አይተው ያደነቁት ነው።

የቅርብ ጊዜ የተቋሙ የ2016 የኦዲት ሪፖርት ተሠርቶ ትርፋማነቱና አዋጭነቱ ተረጋግጦ ለሽያጭ የቀረበ አክሲዮን መሆኑን ጠቁመው፤ አክሲዮኑን የሚገዙ ኢትዮጵያውያን በቀጣይ ልክ እንደጡረታ ገንዘብ ትርፋቸውን እየተቀበሉ እራሳቸውን የሚጠቅሙበት ዕድል መቅረቡን ይገልጻሉ።

ዶክተር ብሩክ እንደሚያመላክቱት፤ የአክሲዮን ሽያጩ የካፒታል ገበያን አሠራርና የሕግ ማዕቀፎችን ያሟላ ነው። ኢትዮ ቴሌኮም ተደራሽነቱን የማስፋት አቅም ያለው፣ የወደፊት የተሻለ ተስፋና ራዕይ ያለው ተቋም በመሆኑ ማህበረሰቡ ድርሻውን በመግዛት ሊጠቀም የሚችልበት ዕድል ሰፊ ነው።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ኃላፊ ሃና ተኸልኩን በበኩላቸው፤ ኢትዮ ቴሌኮም ያቀረባቸውን የካፒታል ገበያ ምዝገባ ሰነዶች በዝርዝር መታየታቸውን ያስረዳሉ።

ኢትዮ ቴሌኮም በመጀመሪያ ዙር 10 በመቶ የባለቤትነት ድርሻን ለኢትዮጵያውያን በመሸጥ ሥራ እንደሚጀምር በገለጸው መሠረት የመደበኛ አክሲዮን ሽያጭ ለማከናወን ኩባንያው ከልማት ድርጅትነት ወደ አክሲዮን ማህበርነት መቀየሩን ነው ያስታወቁት። ሰኔ ወር ውስጥ 2016 ዓ.ም በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት በአክሲዮን ማህበርነት መመዝገቡንም አስታውሰዋል።

በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን በጸደቀው የደንበኛ ሳቢ መግለጫ (prospecctus) የወጡ መስፈርቶችን የሚያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ግለሰብ መደበኛ አክሲዮኖችን ገዝቶ እንዲጠቀም አስፈላጊው የሕግ ድጋፍ መመቻቸቱን ይጠቁማሉ።

በመሆኑም የካፒታል ገበያ የሕድ ድጋፍ ስጋት እንደማይኖር ተናግረው፤ ኩባንያው በኢትዮጵያ ስነደ መዋዕለ ንዋይ የመካተቱ ሂደት ሲጠናቀቅ የተገዙ መደበኛ አክሲዮኖች የመሸጥ፤ የመተላለፍና ከማንኛውም መደበኛ አክሲዮን ወደ ሌላ ባለቤትነትን ማስተላለፍ እንደሚቻል ያስረዳሉ።

የአክሲዮን ገዥዎችን የኩባንያው ባለቤትነት ፍትሐዊነት ለማረጋገጥና የህብረተሰቡን ተሳትፎውን ከፍ ለማድረግን የቀረቡትን የአክሲዮን ግዢ ጥያቄዎች የመደልደል ኃላፊነት የኩባንያው መሆኑን ነው ያስታወቁት።

ኩባንያው በአሁኑ ጊዜ 79 ሚሊዮን የቴሌኮም ደንበኞችን ከማፍራት ባሻገር በሀገር አቀፍ ደረጃ ግዙፍ መሠረተ ልማቶችን በመገንባት ላይ ያለ ትርፋማ ድርጅት በመሆኑ አክሲዮኑን መግዛት አዋጭ ነው የሚሉት ደግሞ የኢትዮ ቴሌኮም ኃላፊ ፍሬሕይወት ታምሩ ናቸው።

ኢትዮ ቴሌኮም የቴሌብር ዲጂታል ክፍያና ሞባይል ገንዘብ አገልግሎትን በማሳለጥ 50 ሚሊዮን ደንበኞችን ማፍራቱን ጠቅሰው፤ በዘርፉ አዳዲስ አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ የኢትዮጵያን የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ በማፋጠን ላይ ያለውን ተቋም አክሲዮን መግዛት አትራፊ ኢንቨስትመንት መሆኑን ያስረዳሉ።

አንድ ግለሰብ ከአክሲዮኑ ዋጋ በተጨማሪ የአንድ ነጥብ አምስት በመቶ የአገልግሎት ክፍያ እንደ ተጨማሪ እሴት ታክስ በመክፈል አክሲዮኖቹን መግዛት እንደሚችል ነው ያስታወቁት።

የባለቤትነት ድርሻው በዋናነት ዘርፉ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ሚና የበለጠ ለማስፋት፣ የኩባንያውን ውጤታማነት ለማሻሻል፣ ካፒታል የሚያገኝበትን ዕድል ለማስፋትና ተቋም የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ጥራትና ተደራሽነት ይበልጥ ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል ይላሉ።

ኃላፊዎቹ እንደሚናገሩት፤ እያንዳንዳቸው 300 ብር የሆኑ 100 ሚሊዮን አክሲዮኖችን በመሸጥ የሚገኘው ገቢ ለተጨማሪ ልማት የሚውል በመሆኑ አትራፊ የሆነውን ኩባንያ መቀላቀል ውጤታማ ኢንቨስትመንትን እንደማከናወን ይቆጠራል።

# የባሕር በር ጥያቄ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ወደ ውጭ የሚልኩትንም ሆነ ወደ ሀገር የሚያስገቧቸውን ምርቶች፣ መሣሪያዎች እና የተለያዩ ግብዓቶች ሚስጥራዊነታቸውን ከሶስተኛ ወገን በተጠበቀ ሁኔታ መላክና ማስገባት ያስችላቸዋል ነው ያሉት።

የባሕር በር አለመኖር ብሎም ወደብን በከፍተኛ ወጪ መከራየት የሀገር ውስጥ ምርት መጠንን፣ የውጭ ምንዛሪ ገቢን በከፍተኛ ሁኔታ የሚጫን መሆኑ ላይ የሚያሰምሩበት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ፣ ጫናው በሀገር ውስጥ በየትኛውም ዘርፍ በሚደረጉ የልማት እንቅስቃሴዎች ሁሉ ላይ የሚያርፍ ነው ይላሉ።

በ2003 ዓ.ም በያዕቆብ ኃይለማርያም የተጻፈው አሰብ የማናት (የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ) መጽሐፍም እንደ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆኑ ሀገሮች ከዋና ዋና የገበያ ማዕከሎች የተገለሉና ከገበያ የራቁ መሆናቸውን አንስቶ፣ ወደብ አልባነት ለኢኮኖሚያዊ እድገታቸው ማነቆ እንደሆነባቸው ይገልጻል። ወደብ አልባ በመሆን ብቻ የአንድ ሀገር የወጪ ንግድ መጠን ከ33 ከመቶ እስከ 43 ከመቶ ሊቀንስ እንደሚችልም ያስረዳል።

ለአንድ ሀገር ልማት አስፈላጊ ከሆኑ ዋነኞቹ ግብዓች መካከል አንዱ ከውጭ ወደ ሀገር የሚገባውና በሥራ ላይ የሚውለው ገንዘብ የውጭ ምንዛሪ መሆኑን የሚጠቅሰው መጸሐፉ፤ አንዲት ሀገር ይህን አስፈላጊ ግብዓት ማግኘት የምትችለው የምታመርተውን ምርት ወደ ዓለም ገበያ ማዝለቅ ስትችል መሆኑን ያነሳል። ወደብ ደግሞ ለዚህ ወሳኙ ድልድይ መሆኑን በማስረዳት፣ ወደብ አልባነትም ሆነ ከወደብ የራቀ ሀገር መሆን የሀገር ምርትን በቀላሉ ወደ ዓለም ገበያ ለማቅረብና አስፈላጊውን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት አሉታዊ ተጽዕኖን የሚያሳድር መሆኑን ያብራራል።

አቶ አያል ሰው ደሴ ከዛሬ 14 ዓመታት በፊት "የባሕር በር ጥያቄ ከኢትዮጵያ አንድነት፣ የሕዝብ ሉዓላዊነት፣ ከፀጥታ፣ ከልማትና እድገት ዋስትናነት አኳያ" በሚል ርዕስ ባስነበቡት መጣጥፋቸው፣ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የባሕር በር አስፈላጊነትን የሚያዩት ከንግድ እንቅስቃሴ መተላለፊያት ባለፈ የቆየ ታካቸውን፣ ያሉብን አስቸጋሪና ፈታኝ አካባቢያዊ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች እንዲሁም ከውጭ ለሚሰነዘር ጥቃትና ቀጥተኛ የእጅ አዙር የባዕዳን ጫና መጋለጥን፣ ከሀገራቸው አንድነት፣ ከአስተማማኝ ሠላምና መረጋጋት፣ ከምጣኔ ሀብት እድገትና ብልጽግና እንዲሁም ከወደፊት ትውልዶች ዘለቄታዊ ጥቅም አኳያ በማየትና በማገናዘብ መሆኑን አስረድተዋል።

ከዘርፈ ብዙ ጠቀሜታው አኳያ የባሕር በር ጥያቄን አጠናክሮ መቀጠል ለነገ የማይባል መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑ ላይ አጽንዖት ሰጥተው የሚናገሩት ወገኔ (ዶ/ር)፣ ኢትዮጵያ እያነሳች ያለችው የባሕር በር ጥያቄ የጋራ ተጠቃሚነት መርህን መሠረት ያደረገ መሆኑ ላይ ያሰምሩበታል። በተጨባጭም ኢትዮጵያ በአቅራቢያዋ ባለው የባሕር በር ተጠቃሚ ብትሆን ለጎረቤት ሀገራት መልካም እድልን የሚፈጥር ነው ያሉት ዶ/ሩ።

አንዲት ሀገር የባሕር በር ተጠቃሚ ስትሆን እንደ መንገድ፣ የኃይል አቅርቦትና መሠል የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎችን ታካሂዳለች፣ የንግድ ልውውጥ እንቅስቃሴም ይጨምራል፤ የአካባቢውን ደህንነት ለማስጠበቅም መልካም እድልን እንደሚፈጥር ይናገራሉ።

እርሳቸው እንዳብራሩት፣ በሀገራት ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ላይ የተደረጉ ጥናቶች የአንድ ሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገት ለጎረቤት ሀገራት ማደግ ድርሻ እንዳለው ያነሳሉ። የአንዲት ሀገር ሠላም ማጣት በጎረቤት ሀገራት የሠላም ሁኔታ ላይ አሉታዊ ጫናን እንደሚያሳርፈው ሁሉ አንዲት ሀገር የባሕር በር ተጠቃሚ በመሆኗ የሚኖራት ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በጎረቤቿ እድገት ላይ በጎ ሚና ይኖረዋል።

ወገኔ (ዶ/ር) እንዳሉት፣ በሀገራችን ማደግና መበልጸግ ላይ መልካም አመለካከት የሌላቸውና ሕዝባቸውን ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መምራት የተሳናቸው ሀገራት የሌለው እድገት ስጋት ውስጥ ይከታቸዋል ያሉት ምሁሩ፣ ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎችን በመሥራት እንዲህ ያሉ ሀገራት ሊፈጥሩ የሚችሉትን ችግር አስቀድሞ መከላከል ያሻል።

በተለይም መንግሥት ውጤታማ የሕዝብ ለሕዝብ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎችን መሥራት፣ ዓለም አቀፍ ሕጎችና ታሪካዊ ዳራዎችን ማስረዳት ከቻለ፣ ፀጥታን ማጠናከር ከሚችል ጠንካራ ኃይል ጋር በመሆን ሀገራችን እንዳትለማና የባሕር በር ተጠቃሚ እንዳትሆን እንቅፋት ሊሆኑ የሚጥሩ ኃይሎችን ወደ ኋላ መመለስ ይቻላል የሚል አስተያየት ይሰጣሉ።

የባሕር በር ጥያቄ ስኬት እስኪያገኝ ድረስ በጋራ የምንታገልለት ፍሬውንም ለትውልድ የሚሆን ጥያቄ እንጂ የመንግሥት ጉዳይ ብቻ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም ያሉት ምሁሩ፣ የባሕር በር ተጠቃሚነት የሚያተርፍልን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በአጭር ጊዜም ይሁን በረጅም ጊዜ እያንዳንዱ ዜጋ ላይ ለውጥ የሚመጣ መሆኑን እንደ ሕዝብ ግንዛቤው ሊኖረን፤ ለስኬቱም በባለቤትነት ልንታገል ይገባልም ሲሉ መልዕክታቸው አስተላልፈዋል።

# "ህንጻዎች ሲገነቡ ጂኦሎጂካል...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ህብረተሰቡ ፎቅ ላይ ካሉ ወደ ኮለን መጠጋት መሬት ላይ ከሆኑ ደግሞ ከኤሌክትሪክ ማማዎች በመራቅ እና ገላጣ አካባቢዎች በመሆን እራሳቸውን ሊጠብቁ እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

እንደ ፍሬወለጋ ገለጻ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ በዚህ ጊዜ ይከሰታል ብሎ መገመት ባይቻልም ጥንቃቄ ማድረጉ ተገቢ ነው፡፡

በሰመራ ዩኒቨርሲቲ የተዋቀረ የጥናት ቡድን የመሬት መንቀጥቀጥ በተከሰተበት አካባቢ በመሄድ ምልከታ ማድረጋቸውን እና በቀጣይም ጥናትና ምርመር በማድረግ ለሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ለማድረስ እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

የአፋር ማህበረሰብ ከቦታ ቦታ እየሄደ የሚኖር ማህበረሰብ በመሆኑ ጉዳት እንዳይደርስባቸው የማስገንዘብ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጨምረው ተናግረዋል፡፡

በአዋሽ ፈንታሌ አካባቢ መስከረም 26 ቀን 2016 ዓ.ም የተከሰተው የመሬት መንቀጥቀጥ በሬክተር ስኬል አራት ነጥብ ዘጠኝ ሲሆን ጥቅምት 3 ቀን 2017 የተከሰተው ደግሞ በሬክተር ስኬል አራት ነጥብ ስድስት መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

የተከሰተው አደጋ የጉዳት መጠንም ዝቀተኛ ነው ያሉት ፍሬ ወለጋ፤ በቀጣይ የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ ምርምሮችን ማድረግ ይገባል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የስምጥ ሸለቆ መገኛ እንደመሆኗ የከፋ ጉዳት ባያደርስም በተለያዩ ጊዜያት የመሬት መንቀጥቀጥ አጋጥሟታል፡፡ በ1900 ዓ.ም ስድስት ነጥብ ሰባት፣ በ1909 ዓ.ም ስድስት ነጥብ ስምንት እንዲሁም በ1961 ዓ.ም ስድስት ነጥብ አምስት በሬክተር ስኬል የተመዘገበ የመሬት መንቀጥቀጥ መከሰቱ የሚታወስ ነው፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሕዝብ የሰላም ጩኸት መልስ አለመስጠት በታሪክ ተወቃሽ የሚያደርግ ከፍ ያለ የልብ ድንዳኔ ነው

ሰላምን በድርድር ለማምጣት፣ ለማስቀጠል እና ለማጽናት የሚደረግ የትኛውም ዓይነት ጥረት የሰላምን ዋጋ በአግባቡ ከመረዳት ፤ ሰላም ማጣት ሊያስከትል የሚችለውን ሁለንተናዊ ጥፋት በሰከነ መንፈስ ከማስተዋል ፤ የየትኛውንም ማህበረሰብ በሰላም የመኖር መሻት በተጨባጭ ከመረዳት የሚመነጭ ከፍ ያለ የዓላማ ጽናት የሚጠይቅ የአስተሳሰብ ከፍታ ነው።

በሰው ልጅ ካለው ግለሰባዊ ማንነት /ሥብእና አኳያ እለት ተእለት ባለው መስተጋብር ውስጥ ከፍጥረታዊ ማንነቱ በመነጨ ልዩነቶች መፈጠራቸው የተለመደ እና ተጋማች እውነታ ነው። የታሪክ መዛግብት አብዝተው እንደሚያመላክቱት ይህ ልዩነት በዘመናት ለመጣባቸው የለውጥ መንገዶች መሠረት ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

እነዚህ ልዩነቶቹ የአስተሳሰብ ብዛህነትን በመፍጠር በመላው ዓለም ለሚገኙ የተለያዩ ወግ ባህሎች መፈጠር ዋነኛ ምክንያት ተደርገው ይወሰዳሉ። የሰው ልጅ አሁን ላይ ፍጥረታዊ ውበቱ አድርጎ ለተቀበለው እና ለሚንከባከበው ህብረብሄራዊነቱ ምንጭ ፤ በማህበረሰብ መካከል ለሚፈጠሩ መስተጋብሮች አቅም እንደሆነ ይታመናል።

በ21ኛው ክፍለ ዘመን እነዚህን የአስተሳሰብ ልዩነቶች በአንድም ይሁን በሌላ ፍጥረታዊ በረከት አድርጎ መቀበል የግድ የሆነበት ዘመን ነው ፤ ዘመኑን መዋጀት የሚቻለውም ከትናንት ስህተቶች ተምሮ የተለያዩ አስተሳሰቦችን አቻችሎ የተሻለ ዓለም መፍጠር የሚያስችል ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት በመፍጠር ነው ።

ከዚህ ውጪ ልዩነቶችን በሃይል ለመደፍጠጥ የሚደረጉ ጥረቶች በቀደሙት ዘመናት ዓለምን ካስከፈሏት ያልተገባ ዋጋ አኳያ አሁን ላይ የጥፋት ሁሉ ምንጭ ፤ በየትኛውም መንገድ የሚወገዝ ፤ የኋላ ቀርነት ከዛም ባለፈ የቆመ ቀርነት መገለጫ የሆነ የአስተሳሰብ ስንኩልነት ነው።

ልዩነቶችን በሃይል ከመደፍጠጥ ይልቅ በልዩነቶች ዙሪያ ቁጭ ብሎ መነጋገር የተሻለች ዓለም ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ አትራፊ እንደሆነ ዓለም ከመቼውም ጊዜ በላይ የተረዳበት እና ለተግባራዊነቱም እየተጋ ያለበት ዘመን ነው። በተለይም የፖለቲካ ልዩነቶችን በድርድር የመፍታት አመራጭ ሰላማዊ ዓለም ለመፍጠር መተኪያ የሌለው አማራጭ ስለመሆኑ ዓለም አሁን ላይ ተጨማሪ አስረጅ የሚፈልግበት ወቅት አይደለም።

የትኛውም ማህበረሰብ በሰላም ለመኖር ካለው ፍላጎት አኳያ የትኛውንም ወደግጭት የሚወስድ ልዩነት በሰላማዊ መንገድ በድርድር ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት ይደግፋል። ይህ ፍላጎቱ በአጋጣሚ የተገኘ ሳይሆን ከሳለፉቸው ሰላም አልባ ዓመታት እና ከከፈለችው ያልተገ ዋጋዎች የተነሳ ነው።

ኢትዮጵያውያንም ከሰላም ጋር በተያያዘ ከተቀረው ዓለም የተለየ ፍላጎት የላቸውም ፤ ለሰላም ካለን ቀናኢነት አኳያ ሰላም የእለት ተእለት የሕይወት መስተጋብራቸው ዋነኛ አጀንዳ ነው። ለዘመናት ከሰላም እጦት ጋር በተያያዘ ከከፈሉት ያልተገባ ብዙ ዋጋ አኳያም አበክረው የሚሹት ጉዳይ ነው።

በተለይም ከሰላም እጦት ጋር በየዘመኑ ብዙ ዋጋ ለመክፈል የተገደደው የሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ሕዝባችን ፤ ጦርነት እና የጦርነት ከበሮ አይፈልግም ፤ ግጭት እና የግጭት ዲስኩሮችን የሚሰማ የተከፈተ ጆሮ የለውም። ከቀደሙት የእርስ በርእስ ጦርነቶች /ግጭቶች ያተረፈው ነገር የለም ፤ወደፊትም ከግጭት እና ከጦርነት ሊያተርፍ የሚችለው አንዳች ነገር አይኖርም።

ትናንት በግጭት እና በጦርነት እራሱን ፤ ልጆቹን እና በልጆቹ ተስፋ ያደረጋቸውን ትናንቶቹን ተነጥቋል። ሀብት ንብረቱ ፤ በብዙ ጣር የገነባቸው መሠረተ ልማቶቹ ወድመዋል። በብዙ የሚመካባቸውን ሀገራዊ እሴቶቹ ደብዝዘዋል፤ የጠላቶቹ ፍላጎት አውቆትም ሆነ ሳያውቀው በላዩ ላይ ተጭኖበታል። በዚህም በድህነት እና ኋላቀርነት ውስጥ ተመጽዋች ሆኖ አንገቱን ደፍቶ እንዲኖር ሆኗል ።

ከዚህ እንደጥላ ከሚከተለው ችግር ለመውጣት ልዩነቶችን አቻችሎ የሚቀበል ሀገራዊ የፖለቲካ ሥርዓት መፍጠር ያስፈልጋል ። ይህ ደግሞ ከዓለም አቀፉ የፖለቲካ ሥርዓት ጋር መቀላቀል ፤ እራስን በዘመኑ እውቀት መዋጀት እንጂ ማነስ አይደለም። የመዘመን ሀሁ እንጂ ፤ጥራዝ ነጠቅነት አይደለም።

ይህንን እውነታ ከሁሉም በላይ ፖለቲከኞቻችን በአግባቡ ሊያጤኑት ይገባል ፤ በትንሹም በትልቁም፤ ጠበንጃ አንግቦ በሕዝብ የሰላም ፍላጎት ላይ በተቃርኖ ከመቆም በፊት ፤ ደግሞ ደጋግሞ ማሰብ በሚያስፈልግበት ዘመን ላይ እንዳሉ፤ ችግሮችን በድርድር ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶች የማነስ ምልክቶች ሳይሆኑ የመዘመን መገለጫዎች መሆናቸውን ሊያስተውሉ ይገባል።

የሰላማዊ ድርድር ጥሪዎችን ተቀብሎ መቆም በራሱ ጀግና የሚፈልግ ፤ የዘመኑ የሕዝብ ወገንተኝነት መገለጫ መሆኑን በተለይም ጠበንጃ አንስተው በየጫካው በገዛ ወገናቸው ላይ የሚተኩሱ ሃይሎች ሊያጤኑት ይገባል ። ወንድሞች እየገደሉ፤ እያገቱ ፤ በብዙ ጣር የተገነቡ መሠረተ ልማቶች እያወደሙ ፤ የሕዝብን የሰላም ፍላጎት የሚንጥ የግጭት ምንጭ እየሆኑ ስለ ሕዝባዊነት ሆነ ወገንተኝነት መናገር አይቻልም። ትልቅ አለማስተዋል፤ መታወር ነው።

ሰላም በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ያለ ሕዝባችን ትልቁ ጥያቄ ነው። ከሰላም እጦት ጋር በተያያዘ እየከፈለ ያለው ዋጋ፤ የግጭትን /የጦርነትን አስከፊነትን ከመቼውም ጊዜ በላይ እንዲያውቅ ፤ ስለሰላም የበለጠ እንዲጮህ እያደረገው ነው ፤ ለዚህ ጩኸት መልስ መሆን አለመቻል በታሪክ ተወቃሽ የሚያደርግ ከፍ ያለ የልብ ድንዳኔ ነው።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከአደባባይ በዓሎቻችን የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን

ምሕረት ሞገስ

የአደባባ በዓሎች የመዝናኛ እድሎች ከመሆናቸውም በላይ አካባቢን ለማስተዋወቅ፣ በሕዝቦች መካከል ታሪካዊና ባህላዊ ትስስር ለመፍጠር ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። ለማህበራዊ ገጽታ እና ለቱሪዝም ዘርፍ እድገት የሚኖራቸው ሚና ቀላል አይደለም። አሁን አሁን በዓላቱ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ውስጥ እንደ አንድ ትልቅ አቅምም እየታዩ ነው።

በዓላትን ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ከፍተኛ አቅም አድርጎ በመጠቀም በኩል የእሲያ ሀገራት፣ በተለይም ቬትናም እና ካምቦዲያን የሚያክላቸው አልተገኘም። እነዚህ ሀገራት በዓላቶቻቸውን በዓለም መድረክ በማስተዋወቅ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ቱሪስት በአደባባይ በዓሎቻቸው ላይ እንዲገኙ በማስቻል ከፍተኛ ገቢ በማግኘት ላይ ናቸው።

ሀገራችን ኢትዮጵያም የተለያዩ የአደባባይ በዓላት ከሚከበርባቸው ሀገራት አንዷ ናት። በዓላቱ ሃይማኖታዊ ባህላዊ እና ማህበራዊ እሴቶቻቸውን ጠብቀው በመቆየታቸው አሁን ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ቱሪስት በመሳብ ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው የገቢ ምንጭ እየሆኑ ነው።

በተለይ በመስከረም ወር የሚከበሩ በዓላት በዋናነት የዓደባባይ በዓት ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በአግባቡ ልንጠቀምባቸው ከቻልን ለሀገሪቱ የቱሪስት ኢንዱስትሪ እድገት ትልቅ አቅም ሊሆኑ እንደሚችሉ አያጠራጥርም። ከእነዚህ በዓሎች መካከል በመስቀል ዋዜማ የሚከበረው የደመራ፣ እሬቻ፣ ፊቼ ጨምበላላ እና የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው ።

በዓላቱ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ የሚሳተፍባቸው፤ በዓለም አቀፍም ሆነ በሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን ሰፊ ሽፋን የሚያገኙ ናቸው። የማህበራዊ የትስስር ገፆችም የበዓሉ አከባበር ዓለም አቀፍ እይታ እንዲኖረው የተሻለ እድል እየፈጠሩ ይገኛሉ። ከኢትዮጵያም አልፎና ተርፎ አንዳንድ በዓሉ የሚከበርባቸውን የሌሎች ኀገራት አካባቢዎች ከማስተዋወቅ ረገድም አበርክቷቸው ሰፊ ነው።

በዓላቱን ለማክበር አደባባይ የሚገኙት ሰዎች፤ አለባበስ፣ አጊያጌያጥ እና በዓሉን የሚያከብሩበት ሥርዓት እና ሁኔታ ለበዓሉ ከፍተኛ ድምቀትን የሚሰጡ ናቸው። ይህን ተከትሎ የበዓሉ ታዳሚዎች አንዱ የሌላውን ባህል እና የበዓል አከባበር ሁኔታ ይመለከታል። እየቆየ ሲሄድ በዓላቱን የራሱ ብቻ ሳይሆን የጋራ ሀብቱ ማድረግ ይጀምራል። ይህ ደግሞ ህብረብሄራዊነትን ከማጠናከር አኳያ የተሻለ እድል ይፈጥራል።

**ይህን ተከትሎ የበዓሉ ታዳሚዎች አንዱ የሌላውን ባህል እና የበዓል አከባበር ሁኔታ ይመለከታል:: እየቆየ ሲሄድ በዓላቱን የራሱ ብቻ ሳይሆን የጋራ ሀብቱ ማድረግ ይጀምራል:: ይህ ደግሞ ህብረብሄራዊነትን ከማጠናከር አኳያ የተሻለ እድል ይፈጥራል**

የመስቀል ደመራ በዓል አክባሪዎች ምንም እንኳ ክርስቲያኖች ይሁኑ እንጂ፤ ከተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የተውጣጡ ሰዎች የሚሳተፉበት ነው። በዚህ በዓል ላይ በተለያዩ ቋንቋዎች መዝሙሮች ይዘመራሉ። አንዱ ከሌላው ጋር ይተዋወቃል። በኢሬቻም ሆነ በፍቼ ጨምበላላ ያለውም ከዚህ የተለየ አይደለም ።

በዓላቱ ከማህበራዊ ፋይዳቸው ባለፈም ለሀገር ኢኮኖሚ የሚኖራቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። የበዓሉ አክባሪዎች በበዓሉ ቀን የሚለብሱትን ልብስም ሆነ የሚጠለቅ ጌጣ ጌጥ ይገዛሉ። ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ከትራንስፖርት አገልግሎት ጀምሮ የተለያዩ ወጪዎችን ያወጣሉ።

በዓሉን ለማክበር ከቦታ ቦታ ከተንቀሳቀሱ በዓሉ በሚከበርበት አካባቢ የሚቆዩበት ሁኔታ ስለሚፈጠር፤ ከሆቴል ምግብ እና መጠጥን አገልግሎት ከማግኘት ባሻገር እየተዝናኑ እግረ መንገዳቸውን የሚጠቀሙባቸውን ቁሳቁሶችን ይሸምታሉ። ሰፊ ሸመታን ማከናወናቸው ደግሞ በዓሉ በሚከበርበት ቦታ ላይ የሚኖረውን የገበያ እንቅስቃሴ እንዲነቃቃ ያደርገዋል። “የሀገር ውስጥ ቱሪዝም” ማለትም ይሄው ነው።

የዓደባባይ በዓሎች ከላይ ከዘረዘርናቸው በተጨማሪ የበዓሉ አክባሪዎች በዓሉ ላይ በመሳተፋቸው እንዲዝናኑ ከማስቻል ጎን ለጎን መንፈሳቸውን እንዲያድሱ እና ከበዓሎቹ በኋላ ሥራቸው ላይ ውጤታማ እንዲሆኑ እንደሚረዳቸውም የሥነ ልቦና ባለሙያዎች ይጠቁማሉ። ከአሰልቺ የሥራ አካባቢዎች ርቀው በዓል እያከበሩ የተለየ ቦታ ከቤተሰብ ጋር ማሳለፍ የሚኖረው ደስታ እና የሚፈጥረው ስሜት የበዓሉ ታዳሚዎች እንዲነቃቁ እና ከመደንዘዝ እንዲላቀቁም እንደሚያስችል ይነገራል።

ምንም እንኳ የአደባባይ በዓሎቹ በተለይም ለሀገር ውስጥ ጎብኚዎች እንዲሁም ለበዓሉ አክባሪዎች ጥቅም እያስገኙ ቢሆንም፤ የተሻለ የቱሪስት መስህብ ሆነው አሁን እንደሀገር ከሚያስገኙት የኢኮኖሚ ጥቅም በላይ ሀገርን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚያስችሉ ይታመናል።

በቱሪዝም ዘርፍ የተሻለ አቅም ለመፍጠር፣ የመንገድ እና የቱሪዝም መሠረተ ልማቶችን ማስፋት፣ የኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂዎችን በጥራት እና በፍጥነት ማግኘት የሚያስችል አቅም መፍጠር፣ የቱሪዝም መዳረሻ ሥፍራዎችን በአግባቡ ማስተዋወቅ . . . ያስፈልጋል ።

አሁን አሁን በአዲስ አበባ በኮሪደር ልማት መንገዶች እና የተለያዩ የመዝናኛ ሥፍራዎች እየተገነቡ ቢሆንም፤ ጊዜውን የሚመጥኑ፣ ጥራት ያላቸው አማራጭ መንገዶችን መገንባት አስፈላጊ ነው። ግንባታው ከአዲስ አበባ አልፎ በክልሎች፤ በተለይም የቱሪዝም መዳረሻ በሆኑ አካባቢዎች አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል።

የአደባባይ በዓላት ሲታሰቡ የመሠረተ ልማት ጉዳይም ስትራተጂክ በሆነ መንገድ ሊታሰብበት የሚገባው መሠረታዊ ጉዳይ ነው።

ከቴክኖሎጂ አገልግሎት፤ በተለይም ከኔትወርክ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በክልል ከተሞችም በጥራት እና በፍጥነት ማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ ጥራት ያለው አገልግሎት የሚሰጡ የሆቴል እና የጤና ተቋማትን በየቅርብ ርቀቱ እንዲኖር ማስቻልም ያስፈልጋል።

የአደባባይ በዓሎችን በአግባቡ ማስተዋወቅ ከዘርፉ የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን ወሳኝ የሆነ ሀገራዊ የቤት ሥራችን ነው። ለዚህም በዋናነት ከቱሪዝም ጋር ተያይዞ ሃላፊነት የተሰጣቸው የመንግሥት ተቋማት የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ። የሆቴል ባለቤቶች፣ አስጎብኚ ድርጅቶች፣ ዘርፉን ማእከል አድርገው ባለሙያዎችን በማፍራት ላይ የሚገኙ የትምህርት ተቋማት እና መላው ሕዝብ/እንግዶችን በሰላም እና ፍቅር በመቀበል የሚጠበቅበትን ሃላፊት መወጣት ይኖርበታል። ሰላም!

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የናይል የቅኝ ግዛት ውሎች ግብዓተ መሬት ተፈጸመ

የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ የናይል ወንዝን የቅኝ ግዛት ስምምነቶችና ውሎች በተግባር የሻረ ማርሽ ቀያሪ የ21ኛው መክዘ ክስተት ከመሆኑ ባሻገር ከቡድ ዲፕሎማሲያዊ ድል ነው። የናይል ወንዝ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ወደ ሥራ መግባት በቅኝ ግዛት ውሎች የሬሳ ሳጥን ላይ ለመጨረሻ ጊዜ የተመታ 12 ቁጥር ምስማር ነው። ለዚህም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፤ “የናይል ወንዝ የትብብር ማሕቀፍ ስምምነት ወደ ተፈጻሚነት መግባት የዓባይን ውሃ ፍትሐዊ እና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀም የተደረገው ረጅም ጉዞ ፍጻሜ ነው፡፡” ያሉት።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶ/ር ኢ/ር ሀብታሙ ኢተፋ በበኩላቸው እንዳስታወቁት ፤ የናይል ወንዝ ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ በናይል ወንዝ ተፋሰስ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በጣም ብዙ ሀገራትን ያሳተፈ የሕግ ማሕቀፍ መፈረሙ ደስታው ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የተፋሰሱ አባል ሀገራት ነው። የስምምነት ማሕቀፉ ላለፉት አስርት አመታት በርካታ ሂደቶችን አልፎ ነው ከጥቅምት 3/2017 ዓ.ም ጀምሮ ሕጋዊ ማሕቀፍ ሆኖ የሚተገበረው። ማሕቀፍ የሁሉንም የተፋሰሱ ሀገራት ፍትሐዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ቢሆንም ኢትዮጵያ ደግሞ ለናይል ወንዝ እያበረከተችው ባለው አስተዋጽኦ ልክ ተጠቃሚነቷን ያረጋግጣል፡፡

የሕግ ማሕቀፍ ስምምነቱ በ45 አንቀጾች የተደገፉ አስራ አምስት ዋና ዋና መርሆዎች ያሉት ሲሆን፤ ከመጠቀም መብት ጋር የተገናኙ፣ የውሃ ሀብት ጥበቃን፣ ተፋሰሱን በመንከባከብና በማልማት ዘላቂነት ያለው አገልግሎት እንዲሰጥ የማድረግ ኃላፊነትንና አስገዳጅነትን ለሁሉም የተፋሰሱ ሀገራት የሚሰጥ ሥርዓትን፤ እንዲሁም የተፋሰሱ አባል ሀገራት በተፋሰሱ ላይ ያሉ ማንኛውንም መረጃዎች በመለዋወጥ እንዲሰሩ የሚደነግጉ አንቀጾችን የያዘ ነው፡፡

ነባር የቅኝ ግዛት ስምምነቶች ፍትሐዊ ያልነበሩና የታችኛውን ተፋሰስ ሀገራት ማለትም የሱዳንና ግብፅን ተጠቃሚነት ብቻ የሚያረጋግጡ ከመሆናቸው ባሻገር፤ በተለይም ኢትዮጵያ ለናይል ወንዝ ከ85 በመቶ በላይ አበርክቶ እያደረገች የቅኝ ግዛት ውሎች ግን እሷን ያገለሉ ብቻ ሳይሆን እፍኝ ውሃ እንዳትጠቀም የሚደነግጉ ነበሩ። የትብብር ማሕቀፉ ግን ይሄን አድሎአዊ አሰራር በመሻር ፍትሐዊ አጠቃቀምን የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል።

የናይል ተፋሰስ የትብብር ማሕቀፍ ከጥቅምት 3 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ በይፋ ወደ ተግባር ገብቷል። ማሕቀፉ፣ የናይል ኮሚሽንን በማቋቋም የናይል ወንዝ አጠቃቀምና አስተዳደር በሕጋዊና ተቋማዊ ማሕቀፍ እንዲመራ የሚያስችል ነው። ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ፣ ማሕቀፉን ያልፈረሙ ሀገራት እንዲፈርሙ ጥሪ አድርገዋል። የማሕቀፍ ፈራሚዎች ኢትዮጵያ፣ ኡጋንዳ፣ ሩዋንዳ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ታንዛኒያና ቡሩንዲ ናቸው። አበው ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ ስለ ታላቁ ወንዞችን ዓባይ አንዳንድ ነጥቦችን እናነሳሳ።

የዓባይ ወንዝ ተፋሰስ የአፍሪካን አህጉር አንድ አስረኛ ይሸፍናል። በዓለማችን ከምንጩ እስከ ሜዲትራኒያን ባህር ድረስ 6ሺህ 700 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ረዥሙ ወንዝ ነው። የዓባይ ወንዝ ሁለት ታላላቅ ገባሮች አሉት። ከቪክቶሪያ ሀይቅ ተፋሰስ የሚነሳው ነጭ ዓባይና ከኢትዮጵያ ተራራማ ቦታዎች የሚመነጨው ጥቁር ዓባይ ነው። ለዓባይ ወንዝ 77 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ማለትም 86 በመቶ ከእነለም አፈሩ በመገበር ጥቁር ዓባይ እንደ ስሙ ታላቅ ወንዝ ነው። ለራሱ ለጥቁር ዓባይ ደግሞ 49 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ በመገበር ዓባይ ትልቁን ድርሻ ሲወስድ፤ ባሮ አኮቦ ወንዝ 17 ቢሊዮን ሜትር ኩብ እና የተከዜ ወንዝ 11 ቢሊዮን ሜትር ኩብ በዓመት ይገብራሉ። የጥቁር ዓባይ የፍሰት መጠን ከሀገሪቱ አጠቃላይ ፍሰት ግማሽ ከመሆኑ ባሻገር በጠቃሚ ማዕድናትም የበለጸገ ነው። ጥቁርና ነጭ ዓባይ ሱዳን ካርቱም ላይ ይገናኙና ዓባይ /ናይል/ ይሆናሉ።

> “
>
> **የጋራ የሆነውን የውሃ ሀብት በጋራ መጠቀም ሲገባ፤ ግብፅ ግን ከማንኛውም ድርድር በፊት የግርጌም ሆነ የራስጌ ሀገራት የ1959ኙ ስምምነት እንዲቀበሉ ቅድመ ሁኔታ ታስቀምጣለች**

ዳሩ ግን የናይል ወንዝ የስምንት የራስጌ ተፋሰስ ሀገራት ሀብት ጭምር ቢሆንም እስከ ዛሬ በብቸኝነት እየተጠቀሙ ያሉት ግን የግርጌ ተፋሰስ ሀገራት የሆኑት ሱዳንና ግብፅ ነበሩ። የጋራ የውሃ ሀብት ቢሆንም የራስጌ ተፋሰስ ሀገራት እኤአ በ1929 በሱዳንና በግብፅ በቅኝ ግዛት ዘመን በተፈረመ አግላይ ስምምነት የተነሳ መጠቀም አልቻሉም። በእንግሊዝ አይዟችሁ ባይነት በተፈረመው ኢፍትሐዊ ውል መሰረት ለሱዳን 4 ቢሊዮን ሜትር ኩብ፤ የተቀረውን ማለትም 48 ነጥብ 5 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ለግብፅ ጀባ ብሏል።

ይህ የቅኝ ግዛት ዘመን ውርዴ የሆነ ስምምነት ሱዳንና ግብፅ የራስጌ የተፋሰሱ ሀገራትን በድጋሚ በማግለል በራቸውን ዘግተው እኤአ እስከ ተፈራረሙበት 1959 ድረስ የቀጠለ ሲሆን፤ በእብሪት የተወጠረው ይህ ስምምነት፣ “ከግብፅ መንግሥት ፈቃድ ውጭ የውሃ መጠኑን ሊቀንስ የሚችል የመስኖም ሆነ የኃይል ማመንጫ ሥራዎችን በዓባይ ገባሮችና ሀይቆች ላይ መገንባት አይቻልም። “ይህ ግብዝነትንና እብሪትን የሚያሳይ ስምምነት ታዋቂው የግሪክ የታሪክ ሊቅ ሔሮዶተስ “ግብፅ የዓባይ ስጦታ ናት።” የሚለውን ይትበሀል የዘነጋ ነው። እኔ ግን ግብፅ የዓባይ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ስጦታ ናት ብዬ ነው የማምነው።

ጥንታዊ ስልጣኔዋም ሆነ የዛሬ ህልውናዋ ከዓባይ ጋር የተቆራኘ ሆኖ ሳለ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከራስጌ የተፋሰስ ሀገራት ጋር ተቀራርቦና ተባብሮ መሥራቱ ይቅርና የምታሳየን ንቀት ያበግናል። ከግርጌዋ ተፋሰስ ሀገራት ለዛውም ከሱዳን ጋር ስለ ዳግም የውሃ ክፍፍሉ ምክክር ካደረገች ከ15 አመታት በላይ እንደሆናት መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ ፈርኦኖችም ሆኑ የዛሬዎቹ ገዥዎች ምን ያህል ከዘመኑ ጋር የመሄድና መሬት ላይ ያሉ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ለመቀበል ፍላጎቱ እንደሌላቸው ያስረዳል። ሆኖም ውሎ አድሮ ሱዳን የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጥያቄ ማንሳቷ አልቀረም።

የ1929ኙ ስምምነት ላይ እንደገና መደራደር እንደምትፈልግ ግብፅን መወትወት ጀመረች። የ1959ኙ የውሃ ክፍፍል ላይም ጥያቄ ማቅረብ ቀጠለች። የተፋሰሱን ራስጌ ሀገራት ፍትሐዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋገጥ አዲስ ስምምነት መፈራረም ካልተቻለ፤ ሱዳንና ግብፅ በአንድ በኩል፤ ኢትዮጵያና ሰባቱ የራስጌ ተፋሰስ ሀገራት በሌላ በኩል ለግጭት የመዳረግ እምቅ አቅም እንዳለው ቀጣናዊ የውሃ ፖለቲካ ልሒቃን ያስጠነቅቃሉ።

የጋራ የሆነውን የውሃ ሀብት በጋራ መጠቀም ሲገባ፤ ግብፅ ግን ከማንኛውም ድርድር በፊት የግርጌም ሆነ የራስጌ ሀገራት የ1959ኙ ስምምነት እንዲቀበሉ ቅድመ ሁኔታ ታስቀምጣለች። ሆኖም ይህ የግብፅ ቁሞ ቀር ቅድመ ሁኔታ በተፋሰሱ ሀገራት ተቀባይነት አላገኘም። ምክንያቱም ስምምነቶቹ የተፋሰስ ሀገራትን በተለይ ሀገራችንን ያላሳተፉ ከመሆኑ ባሻገር ስምምነቶቹ የመንግሥታቱ ድርጅት እኤአ በ1997 ይፋ ካደረገው የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ድንጋጌ ጋር ይጣረሳሉ። ሆኖም የተፋሰሱ ሀገራት የጋራ የሆነውን የዓባይ የውሃ ሀብት ለማልማት የግብፅ ፍቃድ አያስፈልጋቸውም።

ሱዳንና ግብፅ ዓባይን ለትላልቅ መስኖዎችና የኃይል ማመንጫነት ሲጠቀሙበት በአንጻሩ ሌሎች የራስጌ ተፋሰስ ሀገራት ወንዙን የሚጠቀሙበት ለአነስተኛ ኃይል ማመንጫነት ብቻ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት የጋራ የሆነውን ሀብት በስፋት አልምተው የመጠቀም ፍላጎት ስለሌላቸው ሳይሆን ዓለማቀፍ የፋይናንስ ተቋማት በግብፅ ተፅዕኖ የተነሳ ብድር የመስጠት ፍላጎት ስለሌላቸው ነው። የተፋሰሱ ሀገራት የሕዝብ ብዛት በከፍተኛ ፍጥነት በመጨመር ላይ መሆኑን ተከትሎ የውሃ ፣ የምግብና የኃይል ፍላጎታቸው በእጅጉ እያሻቀበ ነው።

የሚያሳዝነው እነዚህ ፍትሐዊ ያልሆኑ የፋይናንስ ተቋማት ለግብፅ ሲሆን እጃቸው ይፈታል። በዚህም ጭው ባለ በርሀ ግዙፍ መስኖዎችን ፣ ሀገሪቱን ሙሉ በሙሉ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ያደረጉ ትላልቅ የውሃ ኃይል ማመንጫዎችን ገንብተዋል። በስተሰሜን የሱዳንና ግብፅ ድንበር ላይ ግብፅ በዓለማችን ረጅሙን የዓባይ ወንዝ በመገደብ በግዙፍነቱ ከዓለም 3ተኛ የሆነውን የአስዋን ግድብ ገንብተዋል። የአስዋን ግድብ 10 ዓመት ከፈጀ ግንባታ በኋላ እአአ በ1970 ተጠናቋል።

በ1954 ግብፅ ከዓለም ባንክ ብድር፣ ከአሜሪካ ደግሞ እርዳታ ለማግኘት ጠይቃ ተስፋ ተሰጧት የነበር ቢሆንም ከእስራኤል ጋር በገባችበት ውዝግብ የተነሳ ሳይሳካ ቀርቷል። በዚህ የተከፋችው ግብፅ ወዲያው ፊቷን ወደ ሶቪየት ሕብረት በማዞር ባገኘችው ብድር ግንባታውን ማካሄድ ችላለች ። ግድቡ 90ሺህ ሱዳናውያን ከማፈናቀሉ ባሻገር በቅርስነት ተከልለው የነበሩ ቦታዎችም በውሃ ተውጠዋል።

እነዚህ ተፈናቃዮች ከቀዬአቸው 600 ኪሎ ሜትር ርቀው እንዲሰፍሩ ሲደረግ ፤ በግድቡ የተነሳ ከቀዬአቸው የተፈናቀሉ ግብጻውያን ግን 40 ኪሎ ሜትር ብቻ እርቀው እንዲሰፍሩ ተደርጓል። ግብፅ ይህን ግዙፍ ግድብ ስትገነባ ከሱዳን ውጭ ሌሎች ሀገራትን ማማከር አይደለም እወቁልኝ እንኳ አላለችም። ሱዳንንም ያማከረቻት አስባላት ሳይሆን በዜጎቿ ላይ የምትፈፅመውን ግፍ እንድታውቀው ይመስላል።

የአስዋን ግድብ 2ሺህ 100 ሜጋ ዋት በማመንጨት ማለትም ግማሹን የሀገሪቱን የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት ያሟላ ሲሆን ለከፍተኛ መስኖ ልማትም ውሏል። ግብፅ እምቅ የኃይል አማራጭ ቢኖራትም ከውኃ የኃይል ማመንጫዎች ውጭ የመጠቀም ፍላጎት የላትም። አንዳንድ ምንጮች እንደሚጠቁሙት 4 ነጥብ 4 ቢሊዮን በርሜል የነዳጅ ድፍድፍ ክምችት በምድሯ ቢኖርም በቀን እያመረተች ያለው ከ640ሺህ በርሜል በታች ነው።

የተፈጥሮ ጋዝ ክምችቷ ወደ 2 ነጥብ 2 ትሪሊዮ የሚጠጋ ኩም የሚጠጋ ሲሆን እያመረተች ያለው ግን ወደ 60 ቢሊዮን ኩም የሚጠጋ ብቻ ነው። እንዲሁም 547ሺህ 500 በርሜል በቀን የተጣራ ነዳጅ ታመርታለች። ሰፊ የከርሰ ምድር ውሃ እንዳላትም ጥናቶች ያመለክታሉ። ይህ ሁሉ አማራጭ የኃይልም ሆነ የመስኖ ሀብት እያላት መላው ስስቷና ቀልቧ ዓባይ ላይ ነው። እሷ የተሻለ አማራጭ ያላት መሆኑን ዓይኔን ግንባር ያርገው ብላ በየአደባባዩ እየማለች፣ እየተገዘተችና እየካደች ፤ ኢትዮጵያ ዝናብን ጨምሮ በርካታ አማራጭ የውሃ ሀብት እያላት ጥቁር ዓባይ ላይ ግድብ የምትገነባው ግብፅን ለማንበርከክና ጂኦ ፖለቲካዊ ሚዛኗን ለመጨመር ነው ስትል በየመድረኩ የአዞ እንባዋን እየረጨች ነው።

ግብፅ የዓባይን የተፈጥሮ ፍሰት በመቀየር በረሀውን ለማልማት 30ሺህ 300 ኪሎ ሜትር የመስኖ ቦዮችን ገንብታለች። ከአስዋን ግድብ 300 ኪሎ ሜትር ርቀት ያህል ውሃ በመሳብ ቶሽካ የተባለውን ሰው ሠራሽ ሀይቅ በመገንባት በረሀውን እያለማች ትገኛለች። በአሁኑ ሰዓት ግብፅ 3 ነጥብ 76 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ታለማለች። ከአስዋን ግድብና ከዓባይ ወንዝ ያልተገባ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚነሱ በርካታ ችግሮች እንዳሉ ሆኖ። በትነትና በስርገት የተነሳ በየዓመቱ ከ12 እስከ 14 በመቶ የሚደርስ ውሃ ከግድቡና ከመስኖ ቦዮች ይባክናል። ለመስኖ ከሚያስፈልገው ውሃ በላይ በመጠቀም ማባከንና ጥራት የሌለው የፍሳሽ መውረጃ በግድቡ ላይ ከሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ይጠቀሳሉ።

ከአሜሪካው የካምፕ ዴቪድ ስምምነት በኋላ የግብፅና የእስራኤል ግንኙነት በመሻሻሉ ፤ የወቅቱ የግብፅ ፕሬዝዳንት አንዋር ሳዳት የፍልስጤምና የእየሩሳሌም ችግር የሚፈታ ከሆነ ከዓባይ ወንዝ 365 ሚሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ በየዓመቱ ለእስራኤል ለመስጠት ቃል ገብተው ነበር። ይህ የጂኦ ፖለቲካ የአሰላለፍ ለውጥ በራስጌ የተፋሰስ ሀገራት ላይ ውስብስብ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም።

ሌላዋ የግርጌ ተፋሰስና ጎረቤት ሀገር ሱዳን ግድቦችን ገንብታለች። እአአ በ1926 ሴናርን ለመስኖ፣ በ1936 ጀበል አውሊያ ለኃይል ማመንጫና ለመስኖ ገንብታለች። በ1950 3ኛውንና 420ሺህ ሄክታር መሬት መስኖ የማልማት አቅም ያለው የሮሴሪስ ግድብን እንዲሁም ከእዚህ በተጨማሪ ሌሎች ግድቦችን ገንብታለች። በዚህም በመስኖ መልማት ከሚችለው 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር መሬቷ 1ነጥብ 9 ሚሊዮን ሄክታሩን ማልማት ችላለች። በግብፅና በሱዳን በመስኖ እየለማ ያለ መሬት የዓባይን 86 በመቶ ከምታበረክተው ሀገራችን ጋር ስናስተያየው እዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑ ሊያስቆጨን ይገባል።

ሻሎም ! አሜን።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ለዜጎች ህክምና በቴክኖሎጂ ተደራሽ ለማድረግ እየተጋ ያለው ወጣት

**ክብረአብ በላቸው**

የጤና አገልግሎት ተደራሽነት ለማኅበረሰብ ደህንነት እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት መሠረታዊ አገልግሎቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የጤና አገልግሎት አቅርቦት ሲባል ታዲያ በሽታዎችን የመከላከል፣ የምርመራ፣ እና የክትትል አገልግሎቶችን ያጠቃልላል፡፡

እ.ኤ.አ በ2021 ዓ.ም በተካሄደው የአፍሪካ የጤና አጀንዳ ጉባዔ ላይ በመላው አፍሪካ እስካሁን ድረስ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት መጠን 52 ከመቶ ብቻ መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይኽን ተከትሎም የጤና ባለሞያዎች የህክምና አገልግሎት ለተገልጋዩ ምቹ በሆነ ሁኔታ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ ለሁሉም እንዲደርስ መደረግ አለበት ሲሉ ጥሪ ያቀርባሉ፡፡ በተጨማሪም መንግሥታት በትብብር መሥራት እንዳለባቸውም ያሳስባሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ የጤና አገልግሎቱን ለኅብረተሰቡ ለማዳረስ ባለፉት በርካታ ዓመታት የተከናወኑ ተግባራት ከሞላ ጎደል በገጠር አካባቢዎች ሳይቀር የጤና ኬላዎች እንዲኖሩ አስችሏል። ምንም እንኳን የጤና አገልግሎትን ለኅብረተሰቡ በማዳረሱ ሂደት መሻሻሎች መኖራቸው ቢነገርም አሁንም የሚታይ የተደራሽነት ችግሮች እንዳሉ በተደጋጋሚ ይገለጻል። የጤና አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ አንዱ መንገድ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መጠቀም ስለመሆኑ ብዙዎች ይናገራሉ።

ዶክተር ሲሳይ አበባ ይባላል። ወጣት የህክምና ባለሙያ ነው። በተለያዩ የመንግሥትና የግል የህክምና ተቋማት በሙያው ተሰማርቶ የቆየ ሲሆን በሥራ ቆይታው ከተመለከተው የህብረተሰብ ችግር በመነሳት በቴክኖሎጂ የተደገፈ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት በማሰብ የቴክኖሎጂ ኩባንያ አቋቁሟል።

ኬ.ኤም.ኤስ.ኢ.ቲ.ኤች ኸልዝ ትሬዲንግ ኢ.ማ (ጤናዎ ዲጂታል ኸልዝ) የዲጂታል ጤና አገልግሎት ሰጪ ኩባንያ መሥራች የሆነው ዶክተር ሲሳይ ሲናገር፤ "እንደ ሀገር የዜጎች መሠረታዊ ፍላጎት የጤና አገልግሎትን ማግኘት ነው። ነገር ግን ዜጎች የህክምና አገልግሎት ፈልገው ወደ ጤና ተቋማት ሲመጡ ተገቢውን አገልግሎት ለማግኘት እጅግ ይቸገራሉ፤ በተጨማሪም በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶችን በቀላሉ አያገኙም፡፡ ይህንን ችግር ለማቃለል በማሰብ ነው ወደዚህ ሥራ የገባነው" ይላል

በአዲስ አበባ ከተማ ባደረግነው ጥናት 40 ከመቶ የሚሆኑ የህክምና አገልግሎት ፈላጊዎች ሐኪም አግኝተው ማማከር አይችሉም። 60 ከመቶ የሚሆኑ ሰዎች ደግሞ የታዘዘላቸው መድኃኒት በአቅራቢያቸው ስለማይገኝ ሰዓታትን መድኃኒት በመፈለግ ያባክናሉ የሚለው ዶክተር ሲሳይ በተለይ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች ማለትም በካንሰር፣ በስኳር፣ ደም ግፊት የሚሰቃዩ ሰዎች በከፍተኛ ሁኔታ ለዚህ ችግር የተጋለጡ ናቸው ይላል።

የሀገራችን የጤና ሥርዓት ባሕላዊ ስለመሆኑ የሚናገረው ዶክተር ሲሳይ፤ በህክምና ተቋማት ከፍተኛ አገልግሎት ፈላጊ ስላለ በወረፋ የተጨናነቀ ነው፣ የመድኃኒት አቅርቦት ደካማ ነው፣ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ መንግሥት ከፍተኛ ወጪ እያወጣ ቢሰራም የሚታየው ለውጥ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ከዚህ አኳያ በሀገሪቱ የተሻለ የጤና አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ሥራ መሥራት የውዴታ ግዴታ ነው ይላል።

አሁን ባለው ሁኔታ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ አንድን ሐኪም ለማግኘት በትንሹ ከሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ይፈጃል፤ ታካሚ ከዶክተሩ ጋር የሚኖረው ጊዜ ግን ቢበዛ ከአስራ አምስት ደቂቃ የማይበልጥ ነው። በዚህ ምክንያት የሚባክነው ጊዜ ከፍተኛ ነው የሚለው ዶክተር ሲሳይ፤ በዚህ ቴክኖሎጂ ግን ህክምና የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በጥቂት ደቂቃ ውስጥ የሚያስፈልገውን የህክምና ባለሙያ ማግኘት እንደሚችል ይናገራል።

የከተማ መስፋፋት እየበዛ በሄደ ቁጥር ሰዎች ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች የመጋለጥ ዕድላቸው እየሰፋ ይሄዳል የሚለው ዶክተር ሲሳይ፤ ተላላፊ ባልሆነ ህመም የተያዙ ሰዎች በየቀኑ ወይም በየሳምንቱ አልያም በየወሩ መድኃኒት ይወስዳሉ፤ እነዚህ ሰዎች በዚህ ቴክኖሎጂ ተጠቅመው በቤታቸው ሆነው የሚያስፈልጋቸውን የህክምና ዕርዳታ ማግኘት እንደሚችሉ ይናገራል።

ድርጅቱ ይህንን ቴክኖሎጂ በተለያዩ አማራጮች ይዞ መጥቷል የሚለው ሲሳይ፤ የመጀመሪያው በድረገፅ www/ tena .com መጠቀም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ድምፅን በመጠቀም የሚሰጥ አገልግሎት ነው። ሰዎች



ዶክተር ሲሳይ አበባ

የሞባይል ስልካቸውን በመጠቀም በርቀት ካለ የህክምና ባለሙያ ጋር በመነጋገር የመጀመሪያ የህክምና ዕርዳታ ማግኘት እንዲችሉ የሚያደርግ ነው ይላል።

አንድ ሰው ሐኪም ሲፈልግ ወደ ዌብሳይቱ ወይም የሞባይል መተግበሪያ ውስጥ በመግባት በስፔሻሊቲ ስንት ባለሙያ እንዳለ የስንት ዓመት ልምድ እንዳለው አይቶ፣ የክፍያ መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ ተመልክቶ፣ መቼ አገልግሎት እንደሚሰጡ አውቆ በፈለገው አማራጭ በድምፅ ሆነ በምስል የማማከርና ህክምና አገልግሎት ማግኘት እንደሚችል ይናገራል።

በሌላ መልኩ በዚህ ቴክኖሎጂ የሚሰጠው አገልግሎት አሁን ያለውን የሰዎች በአካል ተገኝቶ ህክምና የመከታተል ሂደትን የሚከተል ሆኖ ነገር ግን ቴክኖሎጂው አካሄዱን በማዘመን የመጣ ነው" ይላል። "ሰዎች የት ጋር ሄደው የሚፈልጉትን ዶክተር ማግኘት እንደሚችሉ አያውቁም በዚህ ቴክኖሎጂ ተጠቅመው ግን የሚፈልጉትን ሐኪም ካገኙ በኋላ ቀጠሮ በመያዝ ሐኪሙ ወዳለበት የጤና ተቋም ሄደው ህክምና ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋል" ይላል።

በተጨማሪም ህክምና ፈላጊዎች ቤት ለቤት የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ከድርጅቱ ያገኛሉ የሚለው ዶክተር ሲሳይ፤ በዘርፉ የበቃ እውቀት ያላቸው ነርሶች በመጠቀም የቤት ውስጥ ህክምና ለሚፈልግ ሰው አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ አንዱ የድርጅቱ ሥራ ነው። በዚህ ሂደት አገልግሎት ፈላጊው በቤቱ ሆኖ ህክምና ማግኘት እንዲችል መንገዱን ቀላል ማድረግ እንደተቻለ ይናገራል።

ይህ ቴክኖሎጂ ህክምናን ተደራሽ በማድረግ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው የሚለው ዶክተር ሲሳይ፤ ማንኛውም የህክምና አገልግሎት ፈላጊ ግለሰብ ወደ 9456 የጥሪ ማዕከል በመደወል የሚፈልገውን አፋጣኝ የህክምና አገልግሎት ማግኘት እንዲችል ታስቦ የተሰራ በመሆኑ በዚህ ረገድ ትልቅ ትርጉም እንደሚኖረው ይናገራል።

ይህ ቴክኖሎጂ ሌላው ፋይዳ ሰዎች አቅማቸውን ባገናዘበ አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻሉ ነው የሚለው ዶክተር ሲሳይ፤ የካርድ እና መሰል ወጪ ሳይኖርበቸው በቀላል ወጪ አንድ ሰው የጤና ሁኔታውን ማወቅ ይችላል፡፡ ከአንድ ዶክተር ጋር ስለጤናው የምክር አገልግሎት የማግኘት ዕድል ያገኛል፡፡ ስለዚህ በትንሽ ወጪ ጤናን ለመጠበቅ የሚያስችል አሰራር እንደሆነ ይናገራል።

"አሁን ባለው የሕይወት ልምምድ ሰዎች ሩጫ ላይ ናቸው" የሚለው ዶክተር ሲሳይ፤ ብዙ ህመምና የጤና እክል እያለባቸው ከዛሬ ነገ ወደ ህክምና ቦታ እሄዳለሁ እያሉ ጊዜ ይወስዳሉ፡፡ በዚህ ሂደት ድንገት ሕይወታቸው ያልፋል፤ ይህ ቴክኖሎጂ ግን የ24 ሰዓት አገልግሎት ስለሚሰጥ ይህንኑ በመጠቀም ራስን ከከፋ ጉዳት መታደግ እንደሚቻል ይናገራል።

እንደ ዶክተር ሲሳይ ገለፃ፤ ኩባንያው ይዞት የመጣው ሌላው ትልቁ ነገር ሀገሪቱ ብዙ ኢንቨስት አድርጋ ያስተማረቻቸው የህክምና ዶክተሮች የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ማስቻሉ ነው ይላል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው እነዚህ ባለሙያዎች በተፈለገው ልክ ሥራ እያገኙ አይደለም፤ አሁን ግን አንድ ዶክተር ሥራ ለመሥራት የግድ ክሊኒክ ወይም ሆስፒታል መገንባት ሳይጠበቅበት በዚህ ቴክኖሎጂ አማካኝነት የራሱን አቅም በማስተዋወቅ ሥራ መሥራት እንዲችል በር መክፈት ተችሏል። ከዚህ ባለፈ ባለሙያው በሚኖርበት አካባቢ ለሚገኝ የህክምና ፈላጊ አገልግሎት በመስጠት የሥራ ዕድል በቀላሉ እንዲያገኝ የሚያደርግ ስለመሆኑ ይናገራል።

የጤና ባለሙያ በዚህ የቴክኖሎጂ መስመር እራሱን ስላስመዘገበ ብቻ ሥራ መሥራት አይችልም የሚለው ዶክተር ሲሳይ፤ እያንዳንዱ የትምህርት ማስረጃና የሙያ ማረጋገጫ ፈቃድ ትክክለኛነት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከጤና ሚንስቴር ጋር በመተባበር እንዲረጋገጡ ይደረግና ከዚህ በኋላ ነው ወደ ሥራ የሚገቡት፡፡ ይህም ተገልጋይ ጥራቱን የጠበቀ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ ረገድ የሚኖረው ትርጉም ከፍተኛ ነው ይላል።

በአሁኑ ወቅት ከ300 በላይ ዶክተሮች፣ 70 ስፔሻሊስቶች፣ ከ60 በላይ ነርሶች፣ 15 የፋርማሲ እና 4 የላብራቶሪ ባለሙያዎች ብሎም የሥነ ልቦናና የአዕምሮ ጤና አማካሪዎች በሲስተሙ ተመዝግበው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ የሚለው ዶክተር ሲሳይ፤ በተቋም ደረጃ ደግሞ ከ267 በላይ ተቋማት ማለትም 5 ሆስፒታል፣ 61 መድኃኒት አከፋፋዮች፣ ከ150 በላይ የፋርማሲ ባለቤቶች በጋራ እየሰሩ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ትልቅ እመርታ ነው ይላል።

ባለፉት አራት ወራት በዚህ ቴክኖሎጂ የጤና አገልግሎት ለማግኘት የተመዘገቡ 42ሺህ ሰዎች አሉ የሚለው ዶክተር ሲሳይ፤ ከእነዚህ ውስጥ 11ሺህ ሰዎች አገልግሎቱን አግኝተዋል፡፡ ነገር ግን አሁንም ካለው ፍላጎት አንፃር የተጠቃሚዎችንም ቁጥር አነስተኛ የሚባል ነው፡፡ ይህንን ለማሳደግ ቴክኖሎጂውን የማስተዋወቅ ሥራ በስፋት መሥራት እንደሚገባ ይናገራል።

የዜጎች ዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከጊዜ ወደጊዜ መሻሻል እያሳየ ቢመጣም አሁንም በሚፈለገው መጠን አላደገም የሚለው ዶክተር ሲሳይ፤ በተለይ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ህክምና ማግኘት እንደሚቻል አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ግንዛቤ የለውም፤ አሁንም አብዛኛው ሰው ባሕላዊ መንገድ ተጠቅሞ ህክምና ማግኘት ነው የሚፈልገው፤ ይህንን ችግር ለመፍታትና አስተማማኝና ተዓማኒነት ያለው ዲጂታላይዝድ የጤና አገልግሎት መስጠት እንደሚያስፈልግ ይናገራል።

የጤና ሚንስቴርን ጨምሮ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ እየሰሩ ስለመሆኑ የሚናገረው ዶክተር ሲሳይ፤ በተጨማሪም በተመሳሳይ የዲጂታል ጤና ዘርፍ ከተሰማሩ ድርጅቶች ጋር በየጊዜው የአገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል በትብብር የተለያዩ ሥራዎችን እየሰሩ ስለመሆናቸው ይናገራል።

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ቴክኖሎጂ መጠቀም ካልቻለች ከመቶ ሃያ ሚሊዮን በላይ ሕዝቧን ማስተማር እንዲሁም በጤናው ዘርፍ ቁጥሩ ከፍተኛ ለሆነ ሕዝብ ህክምና ተደራሽ ማድረግ አትችልም። በግብርናውም ቴክኖሎጂ በመጠቀም መሥራት ካልተቻለ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ መመገብ አይታሰብም፡፡ ትልቅ ቁጥር ያለው ሕዝብ ነው ያለውና ወደ እያንዳንዱ ቤት መድረስ የሚቻለው በቴክኖሎጂ ነው፡፡ ስለዚህ ከምንም በላይ እንደ ሀገር ለዘርፉ ትኩረት መስጠት ግዴታ ነው ይላል።

**ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ቴክኖሎጂ መጠቀም ካልቻለች ከመቶ ሃያ ሚሊዮን በላይ ሕዝቧን ማስተማር እንዲሁም በጤናው ዘርፍ ቁጥሩ ከፍተኛ ለሆነ ሕዝብ ህክምና ተደራሽ ማድረግ አትችልም**

በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ በባህርዳር፣ መቀሌ፣ አዳማና ሀዋሳ ከተሞች ላይ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የጤና አገልግሎት ለመስጠት እቅድ እንዳለ የሚናገረው ዶክተር ሲሳይ፤ በዚህም ለዜጎች የተቀላጠፈ የህክምና አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር ከ5ሺህ በላይ ለሚሆኑ የህክምና ባለሙያዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንደሚሰራ ይናገራል።

መንግሥት በሁሉም ዘርፍ ለሚተገበሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ያለው አመለካከት አበረታችና ይበል የሚያሰኝ ነው የሚለው ዶክተር ሲሳይ፤ ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። ነገር ግን በታችኛው የመንግሥት መዋቅር ከፍተኛ ችግር አለ፤ ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ጀማሪ ድርጅቶች እንደማንኛውም የንግድ ድርጅት ነው አገልግሎት የሚሰጡት፡፡ ነገር ግን ከንግድ ፈቃድና ግብር አኳያ አበረታች የሆኑ አሰራሮች ተግባራዊ መሆን እንደሚገባቸው ተናግሯል።

# የምድር በረከት

## እየተነቃቃ የመጣው የትግራይ ክልል የወርቅ ማዕድን ልማት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በኢትዮጵያ በወርቅ ማዕድን እምቅ አቅም ካላቸው ክልሎች መካከል የትግራይ ክልል ይጠቀሳል። በሀገሪቱ ወርቅ በማምረት በኩል ከሚጠቀሱት ክልሎች መካከልም ይጠቀስ ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ወርቅ አምርቶ ጥቅም ላይ ከማዋል አንጻር በርካታ ችግሮች እንዳሉበት ይገለጻል። ለዚህም በምክንያትነት የሚነሳው በክልሉ ወርቅ በማምረትና ግብይት ሂደት ሊደረግ የሚገባው ቁጥጥርና ክትትል የላለ መሆኑ ነው። ይህም ማዕድኑን ለሕገ ወጥ ዝውውርና ግብይት ዳርጎት ቆይቷል፡፡

የምርትም ሆነ የግብይት ሥርዓቱን ወደ ሕጋዊነት በማምጣት ከዘርፉ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ብዙ ሲሰራ ቆይቷል። ካለፈው ዓመት ጀምሮ ሕገ ወጥነት በተስፋፋበት የወርቅ ልማትና ግብይት ሥራ ላይ በተደረገው ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም በተሰጠ ድጋፍ አበረታች ለውጦች እየታዩ መሆናቸውን የክልሉ መሬት አጠቃቀም አስተዳደርና ማዕድን ቢሮ መረጃ ያመለክታል፡፡

የቢሮው የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ፍስሃ ግርማይ በክልሉ የወርቅ ማዕድን ልማትና ግብይት ላይ በተሰራው የክትትል ሥራና በተደረገ ድጋፍ ለውጦች እየታዩ መሆናቸው ይናገራሉ። በወርቅ ማዕድን በሚታወቁ ወረዳዎች ላይ ትኩረት ተደርጎ በመሥራቱ ለውጦች ማስመዝገብ ተችሏል ይላሉ። በክልሉ በሚገኙ 26 ወረዳዎች ከፍተኛ የወርቅ ክምችት እንዳለ ጠቅሰው፣ የእነዚህ ወረዳዎችና ዞኖች አመራሮች እና ባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲያገኙ መደረጉን ያስረዳሉ። ይህም በየወረዳው ያሉ የወርቅ አምራቾች ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ማስቻሉን ያመለክታሉ። ከዚህ ጎን ለጎን በማዕድን ላይ የሚፈጸም ሕገ ወጥነትን ለመከላከል ጠንካራ የቁጥጥርና የክትትል ሥራም መከናወኑን ይጠቁማሉ፡፡

በክልሉ በ2016 በጀት ዓመት 50 ኪሎ ግራም ወርቅ ለማምረት ታቅዶ እንደነበር አስታውሰው፣ ይህን እቅድ ማሳካት የተቻለው በዓመቱ መጨረሻ አካባቢ ባሉ ሦስት ወራት በተከናወኑ ተግባሮች መሆኑን ይጠቁማሉ። «ለስኬቱ የተደረገው ጠንካራ የክትትልና የግምገማ ሥራ እንደሚጠቀስ ተናግረው፣ በተለይ ወርቅ ላይ ትኩረት መሰራቱ በዓመቱ ለመፈጸም የተያዘውን እቅድ በዓመቱ መጨረሻ ማሳካት ተችሏል» ይላሉ፡፡

በዘንድሮው በጀት ዓመት የአምናውን እቅድ መነሻ ያደረገ እቅድ ተዘጋጅቶ ሲሰሩ መቆየቱን አቶ ፍሰሃ ተናግረው፣ በተያዘው በጀት ዓመት 800 ኪሎ ግራም ወርቅ ገቢ ለማድረግ ታቅዶ እየተሰራ እንደሆነ ይገልጻሉ። ከዚህም ውስጥ 700 ኪሎ ግራም ወርቅ በኢዛና ድርጅት አማካኝነት እንደሚመረት ጠቅሰው፣ 100 ኪሎ ግራሙን ደግሞ በባሕላዊ አምራቾች ለማምረት ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን ያመላክታሉ፡፡

አቶ ፍሰሃ እንደሚሉት፤ በክልሉ በወርቅ ማውጣት ላይ ለመሰማራት ከማዕድን ሚኒስቴር ፍቃድ የወሰዱ ትላልቅ ወርቅ አምራች ኩባንያዎች አሉ። ይሁንና ኩባንያዎቹ እስካሁንም ወደ ማምረት ሥራ አልገቡም። ኩባንያዎቹ የማምረት ፍቃድ የወሰዱበት የማዕድን አካባቢ በጣም ሰፊ ቦታን ያካለለ ነው። ተንቤንን በመሳሰሉ አካባቢዎች የተሰማሩ ኩባንያዎች አንድ ወረዳ የሚያህል ቦታ ይዘው እስካሁን ሥራ አልጀመሩም። ኩባንያዎቹ ወደ ሥራ ቢገቡ ኖሮ የወርቅ ምርትን ከመጨመር ባሻገር ለብዙ የአካባቢው ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ይችሉ ነበር። አሁን በማዕድን ዘርፉ እየታየ ያለውን ሕገ ወጥ አሰራር ወደ ሕጋዊነት ለማምጣትም በጣም የሰፋ እድል ይኖር ነበር።

በዘርፉ ትልቅ ማነቆ ተብለው ከተለዩት ችግሮች መካከል ዋንኛው የእነዚህ በፌዴራል ደረጃ ፍቃድ የወሰዱ ኩባንያዎች በወቅቱ ወደ ሥራ አለመግባታቸው እንደሆነ ያነሳሉ። በአሁኑ ወቅትም የማዕድን ቦታው ምንም አይነት አገልግሎት ሳይሰጥ ፍቃዱን በወሰዱት ኩባንያዎች ተይዞ ይገኛል ይላሉ። ኩባንያዎቹ የያዙትን የማዕድን ቦታ ለሌሎች ማዕድኑን ማልማት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ለመስጠት አለመቻሉንም ያስረዳሉ። «የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ባለሀብቶቹ ፈቃዱን የወሰዱ ከማዕድን ሚኒስቴር ሲሆን፣ ይህን ፈቃድ ክልል መስጠት አሰራሩ ስለማይፈቅድ ቦታውን ለሌሎች ኩባንያዎች መስጠት አልተቻልም» ሲሉም ያብራራሉ። ኩባንያዎቹ በወሰዱት ፍቃድ መሠረት ወደ ሥራ ገብተው ወጣቱ የሥራ እድል መፍጠር ባይችሉም እስካሁን ምንም ዓይነት ርምጃ መውሰድ አለመቻሉንም ያከላሉ፡፡

የተፈጠረውን ችግር የማዕድን ሚኒስቴር በተደጋጋሚ እንዲያውቀው መደረጉን ጠቅሰው፤ ይሁንና ወደ ሥራ የገባ ኩባንያ አለመኖሩን ያመለክታሉ። ይህ አለመሆኑ የማዕድን ሀብቱ በአግባቡ ለምቶ ጥቅም ላይ እንዳይውል ከማድረግ ባሻገር የሀብትና የጊዜ ብክነትን እያስከተለ መሆኑን ያስረዳሉ። ሚኒስቴሩ በጉዳዩ ዙሪያ ጥናት አሰርቶ ያለውን ችግሩ እንዲቃለል ትኩረት ተሰጥቶ መሥራት እንዳለበት ያስገነዝባሉ፡፡

እንደ አቶ ፍስሃ ማብራሪያ፤ ዘንድሮ ወርቅ ለማምረት ሲታቀድ እነዚህን ኩባንያዎች ታሳቢ በማድረግ ነው። ኩባንያዎቹ ወደ ሥራ ካልገቡ በዘርፉ እቅድ ላይ ትልቅ እንቅፋት ይፈጥራል። በባለፈው ዓመት በማዕድን ዘርፉ ለ45 ሺ ዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ፤ ለ48ሺ 955 ዜጎች የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል። በመሆኑም በዘርፉ በተመሳሳይ መንገድ የሥራ እድል መፍጠር ያስፈልጋል። የሥራ እድል መፍጠር ሲቻል ሕጋዊ አሰራሮች የመከተሉ ሁኔታ እየተሻሻለ ይመጣል፤ ይህ ታሳቢ ተደርጎ በትኩረት በመሥራቱ አፈጻጸሙም ጥሩ መሆን ችሏል፡፡

የቢሮው መረጃ እንደሚያሳየውም፤ ክልሉ ባለፈው በጀት ዓመት በማዕድን ዘርፉ ከአገልግሎት፣ ከመሬት ኪራይ፣ ከሮያሊቲ ክፍያ በክልልና በወረዳ ደረጃ ገቢ የሚያስገኙ ሥራዎችን ለመሥራት ታቅዶ ሲሰራ ቆይቷል። በዚህም በክልል ደረጃ 10 ሚሊዮን ብር፣ በወረዳ ደረጃ ደግሞ 18 ሚሊዮን ብር በአጠቃላይ 28 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ ነበር። በዚህም በክልል ደረጃ ከ11 ሚሊዮን በላይ ብር፣ በወረዳ ደግሞ ከ19 ሚሊዮን በላይ ብር በአጠቃላይ ከ31ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

የዘንድሮውን እቅድም ለማሳካት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ሲወጣ የነበረውን ወርቅ ወደ ሕጋዊነት እንዲመጣ ማድረግ ዋንኛው ሥራ ይሆናል። ሕጋዊ የማምረት ፍቃድ የወሰዱትን አምራቾች ሕጋዊ ፍቃድ ከሌላቸው በመለየት ሕጋዊ ፍቃድ ያላቸውና የተፈቀደላቸው እንዲያመርቱና ያልተፈቀደላቸው ደግሞ ከሥራ ውጭ እንዲሆኑ ይደረጋል፤ የክልሉን የማዕድን ክምችት በመለየት በሌሎች ዘርፎች ላይ መሰማራት ለሚሹ ኢንቬስተሮች ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

«በበጀት ዓመቱ ከማዕድን ዘርፉ 35 ሚሊዮን ገቢ ለማግኘት ታቅዷል» ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ይህም ካለፈው በጀት ዓመት አፈጻጸም በአራት ሚሊዮን ብር ብልጫ እንዳለው ይገልጻሉ። ከወርቅ በተጨማሪ የከበሩ ማዕድናት በስፋት ለማምረት መታቀዱን ጠቁመው፤ 60 ኪሎ ግራም ሳፋየር ማዕድን በማምረት ለገበያ ለማቅረብ መታቀዱንም ያመለክታሉ። በክልሉ ብዙ የማዕድናት ዓይነቶች ቢኖሩም በዋንኛነት የውጭ ምንዛሪን ከማስገኘት አንጻር በወርቅና በሳፋየር ማዕድናት ማልማት ላይ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን ነው ያስረዱት፡፡

በበጀት ዓመቱ ለ50 ባለሀብቶች የማምረት ፈቃድ እንደሚሰጥና እነዚህ ባለሀብቶች ወደ ማምረት ሥራ ሲገቡም ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ። በማዕድን ዘርፉ በክልል ደረጃ 172 ሄክታር፣ በወረዳ ደረጃ 2 ሺ 300 ሄክታር መሬት ሥራ ላይ በማዋል ልማቱ እንደሚካሄድ ይጠቁማሉ። በክልሉ ባለፈው በጀት ዓመት በማዕድን ዘርፍ ኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ አካላት ፈቃድ መሰጠቱን ጠቁመው፤ «ማዕድን ለሚያመርቱ 670 አምራቾች፣ የምርመራ ሥራ ለሚያካሂዱ 499 እና በፈለጋው ለሚሰማሩ 412 ባለሀብቶች ፈቃድ ተሰጥቷል» ይላሉ። ከእነዚህ ውስጥ ከማዕድን ሚኒስቴር ፈቃድ የወሰዱት 35 መሆናቸውን ያነሳሉ፡፡

በማዕድን ዘርፍ ለመሰማራት ፈቃድ ከወሰዱት መካከል ሪፖርት አድርገው ወደ ሥራ የገቡት 127ቱ ወይም 22 በመቶ ያህሉ ብቻ መሆናቸውን አቶ ፍስሃ አስታውቀው፣ ሌሎቹ ምን ዓይነት ደረጃ ላይ እንዳሉ እንደማይታወቅም ይናገራሉ። ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳ ያለው መዋቅር በሰው ኃይልም ሆነ በሌሎች ዘርፉን በሚመጥን መልኩ የተደራጁ አለመሆናቸውን ጠቁመው፤ በወረዳ ውስን የሰው ኃይል ወይም አንድ ሠራተኛ ብቻ ያለበት ሁኔታ እንዳለም ያነሳሉ። በዚህም በዘርፉ የተሰማሩትን ባለሀብቶች ድጋፍና ክትትል ለማድረግ አስቸጋሪ መሆኑን ነው ያመለከቱት፡፡



**በማዕድን ዘርፍ ለመሰማራት ፈቃድ ከወሰዱት መካከል ሪፖርት አድርገው ወደ ሥራ የገቡት 127ቱ ወይም 22 በመቶ ያህሉ ብቻ መሆናቸውን አቶ ፍስሃ አስታውቀው፤ ሌሎቹ ምን ዓይነት ደረጃ ላይ እንዳሉ እንደማይታወቅም ይናገራሉ**

በተያዘው በጀት ዓመት በዘርፉ ያለው የመረጃ አያያዝ በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ለማድረግ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም ዳይሬክተሩ ይጠቁማሉ። እስካሁን ባለው ሁኔታ የክልሉ መረጃ አያያዝ በዘርፉ የተሰማሩ፣ ፍቃድ የወሰዱ እና ፍቃድ ያልወሰዱ አካላት ያልተለዩበት መሆኑን ያስረዳሉ። በመሆኑም በበጀት ዓመት መረጃዎችን የማደራጀቱ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ይናገራሉ። «መረጃውን በማጥራት በዘመናዊ የዳታ አያያዝ ሥርዓት እንዲያዝ ይደረጋል። ዘመናዊ የመረጃ አደረጃጀት መኖሩ ደግሞ እነዚህ በአግባቡ ለይቶ እና አደራጅቶ ለመያዝ ያስችላል» ሲሉ ያብራራሉ፡፡

በክልሉ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ ብዙ የማዕድን ዘርፉ ሀብት መውደሙን ጠቅሰው፤ ይህም ሁኔታ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት በሚፈለገው ልክ አቅማቸውን አጠናክረው እንዳይጠቀሙ እያደረገ መሆኑን ይጠቁማሉ። አሁን በዘርፉ እየሰሩ ያሉት ኢዛናን የመሳሰሉ ድርጅቶችም የህብረተሰቡን ችግር ለመፍታት አቅማቸውን አሟጠው እየተጠቀሙ በኃላፊነት እየሰሩ መሆናቸውን ነው ያስገነዘቡት።

ሌሎች ግን በጦርነቱ ምክንያት በወደመባቸው ከፍተኛ ሀብት የተነሳ አቅማቸው መዳከሙን አስታውቀው፣ እነዚህ ባለሀብቶች ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ያመለክታሉ። ክልሉ ባለበት የአቅም ውስንነት ላይ በዘርፉ የሚታዩ ችግሮች በመደማመራቸው አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ አለመቻሉን ያስረዳሉ። ለእነዚህ ድርጅቶች ድጋፍ በማድረግ አቅማቸውን ማጠናከር ካልተቻለ የተያዘውን እቅድ ለማሳካት እንደሚያስቸግርም ይናገራሉ፡፡

በሌላ በኩል በአመለካከት ረገድም የግንዛቤ ችግር መኖሩን ዳይሬክተሩ ጠቅሰው፤ ወጣቱም ሆነ የተቀረው ህብረተሰብ ሕጋዊነት ተከትሎ መሥራት ላይ ያለው ዝግጁነት ማነስ የዘርፉ ሌላኛው ተግዳሮት መሆኑን ያነሳሉ። በዘርፉ በርካታ የሰው ኃይል፣ ቁሳቁስ እና ቴክኖሎጂ እንዲኖሩ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ያመለክታሉ። በዚህ ረገድ ክልሉ ያለበት ደረጃ እስከታች ድረስ ወርዶ ክትትል ለማድረግ የሰው ኃይል እጥረት እና የትራንስፖርት ችግር መኖሩንም ያብራራሉ። ይህም ሥራውን ለማከናወን አዳጋች እንዳረገውም ነው ያስገነዘቡት፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ ክልሉ ከማዕድን ዘርፉ ማግኘት ያለበትን ገቢ እንዲያገኝ ሕጋዊ መንገድ የተከተለ ሥራ እንዲሰራ መደረግ አለበት። ይህም ሥራ ከአገልግሎትም ይሁን ከሮያሊቲ የሚገኘውን ገቢ ከፍ እንዲል ማድረግን ይጠይቃል። ክልሉም የማዕድን ዘርፉን የሚመራበት ደንብ ያልነበረው ሲሆን ዘንድሮ ይህ ደንብ ወጥቶ ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። ደንቡ ተግባራዊ መደረግ መጀመሩ ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ ከፍ እንዲል፣ ለሥራ አጥ ወጣቶች የሥራ እድል ለመክፈት የበኩሉን ሚና ሊጫወት ይችላል። በክልሉ በማዕድን ዘርፉ ልማት ላይ ለመሰማራት ፍቃድ የወሰዱ ባለሀብቶች ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ ረገድ የማዕድን ሚኒስቴር ትኩረት ሰጥቶት መሥራት ይጠበቅበታል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ሰንፔር

**በትረ ሙሴ (መልክ ኢትዮጵ)**

ለመጀመሪያ ጊዜ መንግሥት ከሚሉት መሥሪያ ቤት ገባሁ። የምሠራበት መሥሪያ ቤት ዓመታዊ እቅዱን በተሳካ አፈጻጸም መከወኑን አስመልክቶ ለተዝናኖት ለሁለት ቀን ከከተማ ወጣ ልንል ሆነ። በደብረዘይት ውበታም ሃይቆች ላይ ቅዳሜና እሁድን ከአናት እስከትቢያቸው አስካካሁባቸው። ቅዳሜ እለት በእለታት ውስጥ የተሰካ ማስተዛዘኛ ካርድ ይመስለኛል። የሆነ ሞገስ አለው.. ሲመጣና ሊመጣ ሲል።

ደብረዘይት እንደቅዳሜ እለት የሆነ መንፈስ አላት.. እንደስሟ ጌታ የተመላለሰባትን የመጽሀፍ ቅዱሷን ትመስለኛለች። በዓመት ለብዙኛ ጊዜ ተመላልሼባት የማትታክተኝ የከንፈር ወዳጄን ናት..፡፡

12 ግድም እግርና ሃሳቤን ተከትዬ አካባቢውን ለመቃኘት ከተያዘልኝ መኝታ ክፍል ወጣሁ። ጽልመት ሊሰፍርበት ያደፈጠበት እለተ ቅዳሜ እሁድን ሊተካ በሽምግልና ያፋሽካል። በነፋሻው የሃይቅ ዳር ለምለም የሚሽኮረምሙ ዘንጣፋ እጽዋቶችን ከሠፈሩባቸው ንቦችና ነፍሳቶች ጋር እየቃኘሁ ለግማሽ ሰዓት ድረስ ተጓዝኩ። እንደበቃኝ ሳውቅ አቅጣጫ ቀይሬ ወደሆነ መንገድ ላይ ተሳፈርኩ።

ቀደም ሲል ወደአፌ አስገብቼ የማላምጠውን የማስቲካ ልባስ በአውራ ጣቴና በሌባ ጣቴ እያድበለበልኩ መልሼ ወደአፌ እከተዋለው። እንደልጅ ቂልነት ሰፍሮብኝ በተሳፈርኩበት መንገድ ርቄ ሄድኩ። ትንሽ እንዳዘገምኩ ከሪዞርቱ መሀል ሰፈር ደረስኩ። በካርድ የሚያገለግሉ የገንዘብ ማሽኖችን ጨምሮ በተለያየ ቀለም የተዋቡ ለመንፈስ ተሀድሶን የሚሰጡ ቅርጻቅርጾችን አየሁ። የራት ሰዓት እየቀረበ ስለነበር ለእራት ከወጡ ከአንዳንድ የመሥሪያ ቤት ሠራተኞች ጋር ተላተምኩ። የሆነ መቆሚያ እስካገኝ አልፌአቸው ሄድኩ። ከፊት ለፊቴ ኮምፒውተር ላይ ያፈጠጠች ቅላቷን ያጎላ ዩኒፎርም የለበሰች ቀይ ሴት የተሰየመችበት አንድ ባዶ ክፍል አየሁ።

እንግዳ መቀበያ ክፍል እንደሆነ መግቢያው በር ላይ በተቀመጠ ደማቅ ጽሁፍ አረጋገጥኩ። ባልባሌ ከምዞር እስከራት ሰዓት ድረስ እንድታዝልቀኝ በዛውም የጉዞዬ ማብቂያ እንድትሆን ፈልጌ ዘው አልኩባት፡፡

እጅግ ሥርዓት በተላበሰ ወግ ለዛውም ከፈገግታ ጋር ‹ጤና ይስጥልኝ እባኮዎ ምን ልርዳዎ? አለችኝ። እባክዎ የምባለው እንዲህ ባሉ ቦታዎች እንደዚች ባሉ ቆነጃጅት ነው። ነገ የሌላቸው እንዲህ ያሉ ማጎንበሶች ያሳቅቁኛል..ቀኔን ነው የሚያበላሹብኝ። ለእኔ አይነቱ እንቡጥ ብላቴና አይደለም ዘገር ይዘው በጉንባሴ ለሚሄዱትም ቢሆን ይሸከኩኛል፡፡

ለንግግሯ ምላሽ አንድ ጥፊ ባልሳትና እዛ ጊቢ ውስጥ ለሚሆነው ለየትኛውም ነገር ራሴን ማዘጋጀት ፈልጌ ነበር። ግን አላደረኩትም፡፡

ማታ ግን ያልታወቀበት የውበት መፍለቂያ ነው። ትንሽ ጨለማ ውስጥ ጥቂት ብርሃን ምን ማለት እንደሆነ ያን ቀን ነው የተረዳሁት። ለእሷም በደነቃት ሁኔታ በጨለማውና በጣሪያው ላይ ብርሃን መሃል ምን እንደምትመስል በማሰብ በዝምታ ብዙ ሰዓታትን ፈጀሁ፡፡

ከቅድሙ ፈገግታና ሳቅ አንዳች ሳታጎድል ‹እባኮ ምን ልርዳዎ› ስትለኝ ከዝምታዬ ጋር ነበርኩ። አማርኛዋን አስተካክላ እስክታናግረኝ በዝምታ ቀጣኋት። ጨለማና ብርሃን ተሳስመው በስመታቸው የነደፉት አንዳች ቀለም ከቀይ መልኳ ስር ሲንፎለፎል አያለሁ። አንድ ሰዓት ጨለማ ላይ ብርሃን ተንጠፍጥፎ ከዛ ጉደኛ ውበት ሌላ ምን ውብ ነገር ሊሠራ ይችላል? አንገቷ ላይ በትንሽ ጨርቅ የተሠራ የሪዞርቱን አርማ ሸብ አድርጋለች። ጣቶቿ የኮምፒውተሩን ቁልፍ ሲጠበጥቡ ይሰሙኛል...በሞዛርት ዘመን ላይ ያለሁ መሰለኝ። ሞዛርት እንደዚች ሴት በጣቶቹ ምት ውብ ዜማን ሲፈጥር ተመሳሰለብኝ። ከሴት የሆነ ሁሉ ለምን ውብ ሆነ? ይቺ ሴት ወንድ ብትሆን ይሄ ሁሉ ዜማ የት ይኖር ነበር? እኔስ በሃሳቤ ጥንተ ሞዛርት ስር ስለምእወድቅ ነበር?

ዜማ ወደሚፈጥሩት ጣቶቿ አተኮርኩ..ሌጣቸውን ናቸው አንዳች ፈርጥን አላሰሩም። ወደመልኳ አሻቀብኩ... ብርሃንና ጨለማ ሻሞ ያሉበት ንጋት መሳይ ጽንሰ ጎህ እድል ፈንታዬ ነበር፡፡

ሥራዋ መለማመጥንም ስለሚጨምር ‹ይቅርታ ጌታዬ ምን ልርዳዎ?› ስትል ከቅድሙ በባሰ አመረረችኝ። በዝምታዬ እሰነብታለሁ ብዬ ነበር..ጌታዬ በምትለው ቅጽል ማስመሰል እንዲህ ስል አፌን ፈታሁ.. ‹እስኪ ረጋ በይ ላንቺም ለሃሳብሽም ቦታ ምረጪ። ውድና ብርቅ ቃላቶችሽን ክብር ለማይገባው ለማንም ወንበዴ እያባከንሽ ነው..› ማለቴን አስታውሳለው..

ያ በጨለማና ብርሃን ስሜት የተፈጠረ መልኳ ጥይምይም አለ። ጨለማ ማለት የብርሃን ጥላ..የውጋግ ኮቴ እንደሆነ ሳውቅና ቀጥዬ ምን ማለት እንዳለብኝ ሳስብ እሷ በመናገር ላይ ነበረች፡፡

‹ይቅርታ..ይሄ ሥራ ቦታ ነው..ልረዳዎት ዝግጁ ብሆንም ለመረዳት ፍቃደኛ አልሆኑም› የሚለው ንግግሯ ጆሮዬ ስተት አለ። ከዛ በፊት የተናገረችውን ለማድመጥ ጊዜን ወደኋላ መመለስ አሰኝቶኝ ነበር፡፡

‹ከኔ በኋላ የሚመጡ ክብርና ሙገሳ የሚሹ ብዙ እንግዶች አሉብሽ ቃላቶችሽን ቆጥቢ እያልኩሽ ነው› በማለት ቁጣዋን ለማለዘብ ሞከርኩ። ለንግግሬ ምላሽ ፈገግታን የጠበኩ ቢሆንም አልፈገገችልኝም። ኮምፒውተሯ ላይ አተኩራ በዜማ ፈጣሪ ጣቶቿ አበሳዬን አየሁ፡፡

ራቴን አሳለፍኩ.. ስለእውነት ርቦኝ ስለነበር የራት ሰዓቴን በጉጉት ስጠብቅ ነበር። አጠገቤ ከእሷ ራቅ ለኔ ቀረብ ያሉ በሥርዓት ያልተደረደሩ ወረቀቶች ይታዩኛል። አተኮርኩበት..አይኔ ‹ሰንፔር› የሚል ስም ላይ አረፈ። ‹ሰንፔር እልፍ ነህ› ከስሙ ጎን አብሮ ስልክ ቁጥር እንዳለ ሳውቅ ደግሞ የበለጠ ረካሁ። የቀይዋን ሴት ዝምታ ተንተርሼ እንደቀልድ በሚመስል እብደት ስልኬን ከኪሴ አውጥቼ ቁጥሩን ስልኬ ላይ መዘገብኩት።

እንግዳ ተቀባይዋን ሴት የመጨረሻ በሆነ የአንድ ጊዜ እይታ ጋር ‹ደህና ያምሹ እመቤቴ› ስል አላግጨባት ወጣሁ። ግን ምን በደለችኝ? በክብርና በትህትና ስለተቀበለችኝ እንደዛ መሆን ነበረብኝ? ራሴን አትረባም እያልኩት ራት ወደሚበላበት አዳራሽ አዘገምኩ።

ሰንፔር ጋ ሳልደውል ሳምንታት አለፉ። የሆነ እለት ደወልኩ..አወራን

ከሁለት ሳምንት የስልክ ማውራት በኋላ በአካል ለመገናኘት ብሄራዊ ቲያትር ቤትን መረጥን፡፡

ማክሰኞ ከሥራ መልስ 11 ሰዓት ላይ ብሄራዊ በር ላይ ቀድሜ ተገኘሁ። እለተ ማክሰኞ ብርሃናማ መልኩን በጸሀይ መግባት ተነጥቆ እከካም መስሏል። ጥላማ ጠይም መልኩን አስግጎ ወደእለተ ረቡዕ ያዘግማል..። ብሄራዊ የሰዎች መናኸሪያ ነው..። አዲስ አበባ ውስጥ ከመርካቶና ከመገናኛ እንዲሁም ከሜክሲኮ ቀጥሎ ብዙ ሰው የሚረግጠው ቦታ ነው። በዚህ የሰዎች ጋጋታ መሃል የማያውቁትን ሰው መጠበቅ ድካሙ ምን እንደሚመስል መገመት አይከብድም። ብቻ አንዲት ውብ ሴት እጠብቃለሁ.. በአእምሮዬና በልቤ የተሳለችን የጀምበር ጉማጅ። ከአራት ማዕዘን ፊት ውጪ ተክለ ቁመናዋን የማላውቃትን ሴት። ያለምክንያት የምትስቅን ነፍስ፡፡

ከቀጠሯችን አምስት ደቂቃ አልፏል..። ወዴት ማየት እንዳለብኝ ሳላውቅ ወደቀናኝ እገላመጣለሁ። ኮቴዋ ያማረ.. በዳናዋ ላይ ሳር የሚያቆጠቁጥባት ሴት እጠብቃለሁ። ድንገት ስልኬ ጠራ..‹የቱጋ ነህ? የሚል ድምጽ ከስልኩ ጉያ ገዝፎ ከጀርባዬ ተሰማኝ። ወደ ኋላ ዞርኩ..የማውቀው ፊት፣ ከማውቀው ፈገግታው ጋር ዊልቸር ላይ ሆኖ በአንዲት ሴት እየተገፋ አየሁት፡፡

ልቤ ሲገፋትና ‹ክብረት? የሚል ጥሪ ስሰማ ባልተዛነፈ እኩሌታ ነበር፡፡

ከነዊልቸሯ አጠገቤ መጥታ ከፈገግታ ጋር እጇን ለሰላምታ ዘረጋችልኝ...

ጨበጥኳት..መዳፏም እንደመልኳና ሳቋ ነው..ለስላሳ። ዝም ብያለሁ..እንደዛ ስቦርቅ የነበርኩት ልጅ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ሰሜን ኮሪያ ያሻሻለችው ሕገመንግሥት ደቡብ ኮሪያን “ጠላት ሀገር” ሲል በየነ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ሰሜን ኮሪያ በቅርቡ ያሻሻለችው ሕገመንግሥት ደቡብ ኮሪያን “ጠላት ሀገር” የሚል ብያኔ ሰጥቷታል።

የሰሜን ኮሪያ ፓርላማ ለሁለት ቀናት መክሮበት ተሻሽሏል የተባለው ሕገመንግሥት ጎረቤት ደቡብ ኮሪያን በጠላት መፈረጁ የኮሪያ ልሳነ ምድርን ውጥረት የሚያባብስ መሆኑ ተነግሯል።

ፒዮንግያንግ በሀገራቱ ድንበር የሚገኝ መንገድን ካወደመች ከሁለት ቀናት በኋላ ነው ሴኡልን በሕገመንግሥቷ በጠላትነት መፈረጇን ያስታወቀችው።

ብሄራዊው የቴሌቪዥን ጣቢያ (ኬሲኤንኤ) ሁለቱን ሀገራት በሚያገናኘው መንገድና የባቡር መስመር መውደሙ ሕገመንግሥቱን እንደማክበር የሚቆጠር ነው ብሎታል። ሕገመንግሥቱ ሴኡልን በጠላትነት መፈረጁን በመጥቀስ። የደቡብ ኮሪያ የውህደት ሚኒስቴር የፒዮንግያንግን ፍረጃ ለአንድነት እና ውህደት የማይበጅ ነው በሚል ተቃውሞታል።

የደቡብ ኮሪያ መንግሥት በፒዮንግያንግ ሊፈጸም ለሚችል ጸብ አጫሪ ድርጊት ፈጣንና ከባድ የአጻፋ ምላሽ ይሰጣል ሲልም አስጠንቅቋል ብሏል አሶሼትድ ፕሬስ በዘገባው።

ተንታኞች ኪም ጆንግ ኡን ደቡብ ኮሪያን በውጭ ጠላትነት መፈረጃቸው የኒዩክሌር መሣሪያዎችን ለመጠቀም ሕጋዊ ድጋፍ ለማግኘት በማሰብ ሊሆን እንደሚችል ያነሳሉ።

ከአሜሪካ ጋር በደቡብ ኮሪያ በኩል ሳይሆን በቀጥታ ለመደራደርም ሴኡልን “ጠላት ሀገር” አድርገው መበየንን መርጠው ሊሆን ይችላል የሚሉ አሉ።

ሴኡል ግን ርምጃው የኪም ጆንግ ኡን አስተዳደር ከዚህ ቀደም የወሰዳቸው ሰላማዊ የውህደት ጥረቶችን ያለመፈለግና ጦርነትን አጥብቆ የመሻት ማሳያ ነው ብላዋለች።

የኪም አስተዳደር ባለፉት ወራት የሁለቱን ኮሪያዎች ውህደት የሚያመላክቱ ሀውልቶች እና የሀገራቱን ግንኙነት ለማሻሻል የተቋቋሙ ተቋማት እንዲፈርሱ ማድረጉ ይታወሳል።

ወጣቱ መሪ ባለፈው ዓመት ጥር ወር ላይ የመልሶ መዋሃድ ፖሊሲው እንዲሰረዝ ማዘዛቸውም አይዘነጋም።

## እስራኤል የሩሲያ እና ቻይና ጸረ ታንክ መሣሪያዎች በሊባኖስ ማግኘቷን ገለጸች



እስራኤል የሩሲያ እና ቻይና ጸረ ታንክ መሣሪያዎች በሊባኖስ ማግኘቷን ገለጸች፡፡

አንድ ዓመት ያለፈው የመካከለኛው ምስራቅ ጦርነት በሰላም ስምምነት ይጠናቀቃል ቢባልም አድማሱን እያሰፋ ይገኛል። የእስራኤል ጦር ከሐማስ ታጣቂዎች ባለፈ ከሊባኖሱ ሂዝቦላህ ጋር የመሬት እና የአየር ለይ ውጊያዎችን በማድረግ ላይ ነው፡፡

የእስራኤል ጦር በደቡባዊ ሊባኖስ እያደረገው ያለው ጦርነት ከጋዛው ጋር ሲነጻጸር ከባድ እና ጉዳቱም እንዳየለበት ተገልጿል። የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ ለኤኤፍፒ እንዳሉት በደቡባዊ ሊባኖስ የሩሲያ እና ቻይና ስሪት የሆኑ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ተገኝተዋል ብለዋል፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስተያየት ከሆነ ሂዝቦላህ በቆፈራቸው የመሬት ውስጥ ዋሻዎች ውስጥ የቻይና እና ሩሲያ ስሪት የሆኑ ጸረ ታንክ መሣሪያዎች ተገኝተዋል፡፡

የመንግስታቱ ድርጅት ጸጥታው ምክር ቤት በፈረንጆቹ 2006 ባሳለፈው ውሳኔ በደቡባዊ ሊባኖስ ከሊባኖስ ብሔራዊ ጦር ውጪ የጦር መሣሪያ መያዝ አልተፈቀደም ነበር ተብሏል።

ሩሲያ እና ቻይና እስካሁን በሂዝቦላህ እጅ ተገኝተዋ ስለተባሉት የጦር መሣሪያዎች ጉዳይ ምላሽ አልሰጡም፡፡

በእስራኤል እና ሂዝቦላህ መካከል እየተካሄደ ያለው ጦርነት አሁንም የቀጠለ ሲሆን እስራኤል ጦርነቱን ለማቆም ከሂዝቦላህ የቀረበላትን የተኩስ አቁም ስምምነት ውድቅ አድርጋለች፡፡

ማህበራዊ

# ሀገርኛ





# ሴራ - የሶዶ ክስታኔ ባሕላዊ የእርቅ ሥርዓት

**ማህሌት አብዱል**

ሴራ ወይም በጎርደና ሴራ የሶዶ ክስታኔ ቤተ ጉራጌ ባሕላዊ የእርቅ ሥርዓት ነው። በሶዶ ክስታኔ በጎርደና ሴራ ጥልቅ የሆኑ ባሕላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ያሉት ሲሆን ከ800 ዓመት በፊት ማህበረሰቡ ይዳኝበት የነበረና አሁንም ድረስ ተጠብቆ የቆየ ባሕላዊ የሽንጎ ሥርዓት መሆኑን ከምስራቅ ጉራጌ ዞን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። የሶዶ ክስታኔ ጉራጌ ሕዝብ ሥራ ወዳድና ታታሪ ሕዝብ ነው ይህ ሕዝብ ከጥንት ዘመን ጀምሮ የወንጀልና የፍትሐ-ብሔር ሕግ ባልነበረበት ራሱን በራሱ የሚተዳደርበት ሕግና ደንብ የጎርደና ሴራ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

የሶዶ ክስታኔ ማህበረሰብ በማህበራዊ ኑሮ በኢኮኖሚያዊ በፖለቲካው የሚያስከትላቸው ችግሮች በመመርመር የኑሮ ቀውስ እንዳይገጥመው በለቅሶ፣ በሰርግ፣ በድንበር ጤናማ ኑሮ እንዳይኖረው የሚከለክለው ሁሉ ባወጣው ባሕላዊ መተዳደሪያ ደንብ መመሪያ መሰረት ሲጠቀምበት ቆይቷል፡፡ማህበረሰቡ አሁንም ድረስ ከዘመናዊ የወንጀል ሕግ ጋር በማይጋጭ መልኩ በጎርደና ሴራ ባሕላዊ መተዳደሪያ ደንብ ይተዳደራል፤ በዚህ ውስጥ ነፍስ ከማጥፋት ወንጀል ጀምሮ ስርቆትና አካል ማጉደልንም ጨምሮ የሚይበት ሁኔታ መኖሩን መረጃው ያሳያል።

ባሕላዊ ግጭት አፈታት ሥርዓት እንደ ሶዶ ክስታኔ እጅግ የሚደነቅ ውስብስብ የሆኑ ጉዳዮችን በማየትና በማስታረቁ ትልቅ ሚና የሚጫወት እንዲሁም ለዘመናዊ ዳኝነቱም እገዛ እንደሚያደርግ የባለጉዳዮችን መጉላላትን እንደሚቀንስ ይታመናል። ይህ ብቻም ሳይሆን ትልቁ ጠቀሜታው እርቁ እውነተኛ እርቅ እንዲሆን ቂም በቀል ሳይያዝ በነፃነት የሚፈፀምበት መሆኑ ነው። በተለይም ከነፍስ ማጥፋት ጋር ተያይዞ የተከሰቱ ወንጀሎችን በሰላማዊና የማህበረሰቡን ማህበራዊ ግንኙነት በማያሻክር መልኩ እንዲከናወን በማድረግ ረገድ የሴራ ሽንጎ ሚና የላቀ እንደሆነም ይጠቀሳል፡፡

በጎርደና የነፍስ ማጥፋት ወንጀል ፍርድ የሚሰጠው በሀገር ሽንጎ ሲሆን ውሳኔው የሚፀናው ደግሞ በወማኖ የሴራ ሽማግሌዎች ነው። በሀገር ሽንጎ የነፍስ ማጥፋት ወንጀል የሚዳኘው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅደም ተከተል መያዝ ይጠበቅበታል። ወንጀል ፈፃሚው በተለያየ ምክንያት ሰው ሊገድል ይችላል፤ አስቦበትና ሆን ብሎ አልያም በስህተት ሊገድል ቢችልም በሴራ ሽንጎ በዝርዝር ተፈትሾ የሚታይበትና ተበዳይም ሆነ በዳይ ፍትሕ እንዲያገኝ የሚያደረግበት ሁኔታ ነው ያለው።

ወንጀል የፈፀመው ወይም ነፍስ ያጠፋው ግለሰብ ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ አካባቢውን ለቆ ቤተሰቡን ሰብስቦ ይሰደዳል። ከቆይታ በኋላ ሽማግሌዎች እርቅ እንዲፈፀም ካህናት፣ ዲያቆናት፣ ልጃገረድ፣ ወጣት ወንድ እና ሌሎች የገዳይ ቤተሰብ ተሰብስበው ወደ ሟች ቤት ሽማግሌዎች ይዘው ሄደው ይለምናሉ። እነዚህ ገዳይን ወክለው የተገኙ ሽማግሌዎች የፈጣሪን ስም በማንሳት የሟች ቤተሰብ ‹‹ይቅር ለእግዚአብሔር›› እንዲሉ ይማፀናሉ። ከሁለት ከሶስት ጊዜ ልመና በኋላ የሟች ቤተሰቦች ሽምግልና ይቀበላሉ፡፡

ይሁንና የሟች ቤተሰቦች እርቁን እሺ የማይሉ ከሆነ ልጃገረድና ወጣት ወንድ ላይ ቀንበር ተጭኖ ከሽማግሌዎቹ

> **በቀጠሮው እለትም የተመረጡ ሽማግሌዎች፣ ገዳይና የሟች ቤተሰቦች በጋራ ወደ ወማኖ ሽማግሌ ሄደው ጉዳዩን በዝርዝር ካስረዱ በኋላ መስተካከል ያለበትን እንዲያስተካክሉ፤ ባለበት የሚፀናውም ባለበት እንዲፀና ተደርጎ እርቁ የፀና እንዲሆን ይደረጋል**

ጋር እንዲሄዱ ይደረጋል። ይህ የሚደረገውም ልመናው ከፍ ያለ መሆኑን ለማመላከት ነው። ከዚህ ሁሉ ምልልስ በኋላ የሟች ቤተሰብ የእርቅ ሥነ-ሥርዓት ከተቀበሉ ወጪ ዘርዝረው እንዲያቀርቡ ቀጠሮ ይያዛል። በቀጠሮው ቀን የገዳይ ቤተሰቦች እና ሽማግሌዎች ብሩን ይዘው የሚቀርቡ ሲሆን፣ ሙሉ እርቅ ለሚፈፀምበት ቀን ደግሞ ሌላ ቀጠሮ ይዘው ይለያያሉ።

በዚህ ቀን በሀገር ሽንጎ ላይ ጉማ ወይንም ካሳ ወይፈን፣ ጊደር፣ አልባሳትና ሌሎችም ቁሳቁስ ይዘው ይመጣሉ። እነዚህ እርቅ የሚያስፈፅሙ ዳኞች በሁለቱም በኩል በገዳይም በሟችም በኩል ይቀመጣሉ። ከዚህ በኋላ በሟች ቤት ድግስ ተዘጋጅቶ ሁሉም በእርቅ የተሳተፉ አካላት በእለቱ ይገኛሉ። ጥቁር በግ ተዘጋጅቶ ገዳይ እራሱ እንዲያርድ ይደረጋል። በበጉ አንጀት የሁለቱ (በገዳይና በሟች ቤተሰብ) አውራ ጣት ላይ ይታሰርና መሀላ እንዲፈፅሙ ይደረጋል። አንጀቱ መሀል ላይ እንዲቆረጥ ይደረጋል። ይህ የሚደረገው ሁለቱ ባለጉዳዮች ቃላቸውን ማጠፍ እንደሌለባቸው ለማመልከት ነው።

ከእርቁ በኋላ ማር፣ ጠላ፣ ቅቤ፣ ቦርዴ እና አስፈላጊ የሆኑ መጠጦች ይቀርባሉ፤ የሟች ቤተሰብ እና የገዳይ ቤተሰብ አንድ ላይ ተሰብስበው ከተቀመጡ በኋላ የተጣለው ጉማ /ካሳ/ ገዳይ ለሟች ቤተሰብ ይሰጣል። በመቀጠልም ሽማግሌዎች መርቀው ገዳይና ሟች በቀረበው ማዕድ እንዲጎራረሱና ቅቤም እንዲቀቡ ይደረጋል። በማግስቱ በገዳይ ቤት በሚዘጋጅ ድግስ ላይ ሁሉም እንዲሳተፉ ይደረግና ከሟችና ከገዳይ ቤተሰቦች ሽማግሌዎች በመምረጥ እርቁን የፀና ለማድረግ ወደ ወማኖ የሴራ ሽማግሌዎች ለመውሰድ ቀጠሮ ይዘው ይለያያሉ።

በቀጠሮው እለትም የተመረጡ ሽማግሌዎች፣ ገዳይና የሟች ቤተሰቦች በጋራ ወደ ወማኖ ሽማግሌ ሄደው ጉዳዩን በዝርዝር ካስረዱ በኋላ መስተካከል ያለበትን እንዲያስተካክሉ፤ ባለበት የሚፀናውም ባለበት እንዲፀና ተደርጎ እርቁ የፀና እንዲሆን ይደረጋል። የወማኖ ሴራ አስፈፃሚዎች በደቡብ ሶዶ ወረዳ የሚገኙ ሲሆን በጎሳ ገንዛደም ይባላሉ።

**የወማኖ ሴራ**

የዞኑ መረጃ እንዳመለከተው፤ የወማኖ ሴራ ‘ራጋ ‘እና ‘ጌፈቼ ሤራ’ የተባሉ ሌላ ሁለት መጠሪያ ስሞች ያሉት ሲሆን ዎማኖ የሚለው ስም የሀገር ሽማግሌዎች የወሰኑት ውሳኔ በትክክል ከጐርደና ሤራ ጋር የተጣጣመ መሆኑን የሚመለከቱ ባሕላዊ ዳኞች ይወክላል። በተለይም የጉዳት ካሳ፣ የወጪ መተኪያና ማካካሻን ለዕርቅ ሥርዓቱ መደረግ ያላባቸውን ባሕላዊ ሥርዓቶች በተመለከተ በትክክል መወሰናቸውን ይከታተላል ወይም ያረጋግጣል። በይበልጥ ደግሞ እውነቱ እንዲወጣና ዕርቁም በዚያው መሠረት መካሄዱን ለማረጋገጥ ጥረት ይደረጋል። በተጨማሪም በአንድ ቤተሰብ ላይ ወይም በአንድ አካባቢ የተከሰተን መከራና ክፉ ነገር ያመጣው ምን እንደሆነ ሚስጥሩን ገልፀው ያወጣሉ፡፡

የዎማኖ ሽማግሌዎች ለአንድ ጉዳይ ማስረጃ ፍለጋ አይሄዱም፤ የሀገር ሽማግሌዎች ባቀረቡት ማስረጃ መነሻነት ውሳኔያቸውን ያስተላልፋሉ። ዎማኖ ከግለሰብ ጉዳዮች አልፎ አሳሳቢ የሆኑ የጋራ ችግሮችን እንደ ሰብል ውድመት፣ የተፈጥሮ አደጋ መቅሰፍት፣ በአንድ አካባቢ የሰዎችም ሆነ የእንስሳት በብዛት ማለቅ ወይም ሌሎች ለየት ያሉ ክስተቶችን ይመለከታል፤ እንዲሁም የአካባቢውን ቀደም ያለ ታሪክ ይመረምራል፤ ይህን አስመልክቶም የሀገር ሽማግሌዎች በጉዳዩ ምን እንዳሉ ይፈትሻል። ይህ የኋላ ታሪክ የማወቁ ጉዳይ ምን ዓይነት ባሕላዊ ሥርዓት ይደረግ የሚለውን ለመለየትና በመጨረሻም (ኬርታ) እንዲካሄድ እስከ መወሰን ድረስ ሊኬድ ይችላል፣

የዎማኖ ሤራ የሚሰጠው (በገንዛደም) ጥብ (ጐሳ) ብቻ ሲሆን አመላመሉም ከገንዛደም ስድስት ሰዎች ይመረጣሉ፤ ከተመረጡት ሰዎች በዕድሜ መብሰል በሂደት የፍርድ ሂደቱን ተግባር ይረከባሉ። ሆኖም በአንድ ጊዜ የሚካሄድ ርክክብ አይኖርም። አንድ የዎማኖ አባል ይህን አገልግሎት የሚሰጠው የግብርና ሥራውን ጐን ለጐን እየሰራ መሆኑም መረጃው ይጠቁማል፡፡

በአሁኑ ወቅት ዎማኖ በኬላ ከተማ በሚካኤል ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ በየወሩ የሚካሄድ መሆኑን የሚያመለክተው የዞኑ መረጃ፤ ማንኛውም ሰው ከየትኛውም ጐሳ፣ ፆታ፣ ሃይማኖት ይምጣ ችሎቱን የመከታተል መብት ያለው መሆኑ ያስረዳል። በዚህ ባሕላዊ የእርቅ ሥርዓት ላይ የቀረበ ማንኛውም ተከራካሪ አካል ውሳኔውንም የሚቀበል ግዴታ አለበት፤ ተፈፃሚም እንደሚሆን ነው የሚያስገነበው። ዎማኖ የሚጀመረው በምርቃት ሲሆን ይህም የሚቀርቡት ጉዳዮች ያለ ምንም አድልኦ ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ለማከናወን እንዲቻል ነው።

**ጌፈቸን**

ጌፈቸን ማለት በሶዶ ክስታኔ ትርጉሙ ይግባኝ ነው አንድ የሳቡኘት አባል በሳቡኘቱ የተወሰነበትን ማንኛውም ቅጣት ያለ አግባብ ነው ወይም ፍርድ ጎሎብኛል የሚል ከሆነ ቅጣቱ እንዲነሳለት በተጨማሪ ለበላይ የሀገር ሽንጎ ሽማግሌ ጌፈቸን (ይግባኝ) ሊል የሚችልበት ሥርዓት መኖሩን መረጃው ያመለክታል። ያቀረበው የጌፈቸን አቤቱታ በሽንጎ ተመርምሮ ወይም ይሻሻልለታል፤ አልያም ደግሞ ሙሉ በሙሉ ሊሰረዝለት የሚችልበት ሁኔታ አለ። ይህ ካልሆነ ደግሞ በሳቡኘት ደረጃ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ሽንጎው ሊያጸናበት ይችላል።

**መገን/መገንታ**

እነዚህ መገን እና መገንታ የተሰኙት ቃላት የመማጸኛ ወይም አንዳንዴ የማውገዣ ቃላት ናቸው። እነዚህ ቃላት በክስታኔ/ጉራጌ ማህበረሰብ ውስጥ በሰፊው የሚሰራባቸው መሆኑን የዞኑ መረጃ ያሳያል። መገን/መገንታ ጥሬ ትርጉማቸው ለምሳሌ በእግዜር መገን ፤ በሳቡኘት መገን፣ በሀገር መገን፤ በእገሌ መገን፤ ትርጉማቸውም በእግዜር አማጽናለሁ ወዘተ እንደ ማለት መሆኑን ያስረዳል። ይህ ማለት አንድ የሳቡኘት አባል ጎረቤቱ ወይም ሌላ አባል በደል ቢያደርስበት በቤተክርስቲያን ሕዝብ በተሰበሰበበት ቆሞ ስም ጠርቶ እገሌ እንዲህ ያለ በደል አድርሶብኛል ሲል በእግዜር መገን ፤ በሳቡኘት መገን፤ በሀገር መገን፤ በእገሌ መገን...ወዘተ ብሎ የሳቡኘት ወይም የሀገር ሽንጎው አይቶ ፍርዱን እንዲሰጠው በቃል የሚጠይቅ መሆኑንም ነው የሚያብራራው።

የእነዚህና ሌሎችም ጥንታዊ እሴቶች ባለቤት የሆነው የሶዶ ክስታኔ ሕዝብ በተለይም በባሕላዊው የሴራ ሥርዓት መንግሥት ባልነበረበት ወቅትም አካባቢና ሀገርን በማስተዳደር ለፍትሕ መስፈን አወንታዊ ሚና የተጫወተ ስለመሆኑ መረጃው ያመለክታል። ይህንን የሚያመላክቱ ሰነዶች አሁንም ድረስ ተሰንደው በብሔረሰቡ ሽማግሌዎች ዘንድ የተቀመጡ መሆናቸውን ይጠቁማል። ለምሳሌ ከካሳ ጋር ተያይዞ ከአንድ የሰውነት ክፍል ጣትን ብንመለከት ለሁሉም ጣቶች እኩል ካሳ እንደማይከፈልና ለጌጥ ተብለው የተለዩት በተለየ መልኩ ክፍያ እንደሚፈፀም ጠቅሶ፤ ይህ ባሕላዊ መተዳደሪያ ደንብ ከአስራ ስድስት ትውልድ በፊት ጀምሮ ሕዝቡ አምኖበት የሚተዳደርበት መሆኑን ያብራራል፡፡

በርካታ የብሔረሰቡ ተወላጆች ይህንን ባሕላዊ የእርቅ ሥርዓት አክብረው የሚጠቀሙበት መሆኑን፤ ከዘመናዊ የፍትሕ ሥርዓት ጎን ለጎን ለአካባቢም ሆነ ለሀገር ሰላም መስፈን የማይናቅ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል። ሆኖም የብሔረሰብ ሽንጎ ምክር ቤት ከዚህ ሴራ መጽደቅ በኋላ የወማኖ ሴራ በተቋም ደረጃ ተቋቁሞና ከሚሰጠውም ትልቅ ሀገራዊና ማሕበረሰባዊ ግልጋሎት በማየት ከመንግሥት ጋር በመሆን ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ መሥራት ያስፈልጋል። ለዚህም የሙያው ባለቤቶች ሰብስቦ ማገዝ ይጠበቅባቸዋል።

በሌላ በኩል የጎርደና ሴራ የሶዶ ማህበረሰቡ ባሕል ታሪክና ቋንቋው ለማሳደግና ለመንከባከብ ብሎም ለማስተዋወቅ አጥፊዎች ለማረም የሚፈጠሩ ግጭቶችንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል የማይተካ ሚና እንዳላቸው አጠያያቂ አይደለም። በመሆኑም በተለይ የማህበረሰቡ ተወላጅ የሆኑ አዳዲስ ትውልዶች ሊጠቀምበትና እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ የድርሻውን ሊወጡ ይገባል ባይ ነን፡፡

# ስፖርት





## “ከአምስት ቀን በኋላ ሥራዬን እለቃለሁ”

*- አሠልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ*

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን (ዋልያዎቹ) በ2025 የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ሦስተኛና አራተኛ ጨዋታዎችን ባለፈው ቅዳሜና ማክሰኞ ከጊኒ ጋር አድርገው በሁለቱም ጨዋታዎች መሸነፋቸው ይታወቃል። በገለልተኛ ሜዳ ኮትዲቯር ላይ በተደረጉት ሁለቱ ጨዋታዎች ዋልያዎቹ 4ለ 1 እና 3ለ 0 በሆነ ውጤት ተሸንፈው ወደ አፍሪካ ዋንጫ የማለፍ ዕድላቸውን አጥበበው ተመልሰዋል።

የዋልያዎቹ አሠልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ በወቅታዊ የብሔራዊ ቡድን ጨዋታዎች ዙሪያ ትናንት በፌዴሬሽኑ ፅህፈት ቤት በሰጡት መግለጫ፣ “ከአምስት ቀን በኋላ ሥራዬን እለቃለሁ” በማለት ከዓመት በፊት የፈረሙት ውል መጪው ጥቅምት 23/2017 ዓ/ም እንደሚጠናቀቅ ጠቁመዋል።

አሠልጣኙ እየተመዘገበ ባለው ውጤት “እንደ አንድ ግለሰብ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ሲሸነፍ ምን ይሰማሃል?” ተብለው በጋዜጠኞች ለተጠየቁት ጥያቄ ሲመልሱ፣ “ኢትዮጵያ ስትሸነፍ ከእናንተ የተለየ ስሜት አይኖረኝም። ከእናንተ በላይ ነው የምቆረቆረው። እኔ ተዋናይ ስለሆንኩ እናንተ ተዋንያን ላትሆኑ ትችላላችሁ፣ እኔ ደግሞ ከማንም በላይ እጎዳለሁ፣ ስሜቱ በጣም ከባድ ነው። የምንችለውን ያህል ነው ጥረት የምናደርገው። መታወቅ ያለበት ተጨባጭ አቅማችንን ማወቅ አለብን። አንዳንድ ጊዜ ስሜታዊ መሆን አያስፈልግም። ከጊኒ ጋር ተጨባጭ የአቅም ልዩነት አለን፣ እንደ ቡድን ጠንካራ ሀገር ነው። በተቻለ መጠን ያለውን ልዩነት አጥብበን ተፎካክረን ለመውጣት ጥረት አድርገናል። ያም ቢሆን የፍጥነት ልዩነት ይጎላል። በተለይ የመከላከሉ ላይ እና ኳስ ስናጣ የምናደርገው እንቅስቃሴ የለም። የምንጫወተው ኳስ ስናገኝ ብቻ ነው። ይህ በጣም መታረም ያለበት ሥራ የሚፈልግ ነገር ነው።” ብለዋል።

አሠልጣኙ በቀጣይ ከብሔራዊ ቡድን ጋር የሚኖራቸውን ቆይታ አስመልክቶ ሲናገሩም “ከአምስት ቀን በኋላ እለቃለሁ፣ ውሉ በሃያ ሦስት ነው የሚያልቀው ምን እንደሚያስጨንቃችሁ አላውቅም። ውሉ ሲጠናቀቅ እለቃለሁ” በማለት ተናግረዋል።

“የኢትዮጵያን ሽንፈት የዓለም ፍፃሜ አታድርጉት” በማለት የተናገሩት አሠልጣኝ ገብረመድህን፣ ቡድናቸው የሥነ ልቦና ችግር እንዳለበት ሲያስረዱ አንድ ግብ ሲያስተናግድ ሌላ ግብ በቀላሉ የማስተናገድ ችግሮች ሲያስረዱ “ተጫዋቾቻችን በየጨዋታው የተለያየ አቋም ማሳየት ትንሽ ችግር ፈጥሮብናል። በዚህ ላይ የሥነ ልቦና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል በአንድ ነገር ቶሎ የመርካት ነገር ይታይባቸዋል።” ብለዋል።

ከአጨዋወት ጋር በተያያዘ ለተነሳላቸው ጥያቄም “አቋሜን አልቀይርም፣ አሁንም ወደ ፊትም ቀጥተኛ አጨዋወት ነው የምጫወተው ፤ ከዚህ በኋላ ምን ያህል ጊዜ ሊኖረኝ ይችላል ? ባለኝ አጭር ጊዜም ቢሆን አልቀይርም ፤ ረጅም ጊዜ አልቆይም ፤ እኔ ባመንኩበት ነው የምቀጥለው። የአጨዋወታችን ስህተት ስለነበረ አይደለም በግልጽ ልዩነት ስላለን ነው የተሸነፍነው፣ ሲሉ አሠልጣኝ ገብረመድህን ገልፀዋል።

በ2025 አፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ዋልያዎቹ በሚገኙበት ምድብ ዴሞክራቲክ ኮንጎ በአራት ጨዋታ 12 ነጥብና ስድስት ግብ ይዛ ትመራለች። ጊኒ በስድስት




ነጥብና አራት ግብ ሁለተኛ ላይ ስትገኝ፣ ታንዛኒያ በአራት ነጥብ ሁለት የግብ ክፍያ ይዛ ሦስተኛ ነች። ዋልያዎቹ በበኩላቸው አንድ ነጥብና ስምንት የግብ እዳ ይዘው የመጨረሻው ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል።

በደረጃ ሰንጠረዡ ሂሳባዊ ስሌት መሠረት ዋልያዎቹ በሞሮኮ በሚካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ ለመሳተፍ ያላቸው እድል ሙሉ በሙሉ ዝግ አይደለም። በቀሪዎቹ ሁለት የማጣሪያ ጨዋታዎች ዋልያዎቹ አሸንፈው ጊኒና ታንዛኒያ ሁለቱንም ከተሸነፉ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ዋንጫው የመብቃት ጠባብ ተስፋ አላት። ዋልያዎቹ በቀጣይ የማጣሪያ ጨዋታዎች የምድቡን መሪ ዴሞክራቲክ ኮንጎንና ታንዛኒያን የሚገጥሙ ይሆናል።

ዋልያዎቹ ከዴሞክራቲክ ኮንጎ ጋር ያደረጉትን የመጀመሪያ ጨዋታ 4 ለ0 በሆነ ውጤት መሸነፋቸው የሚታወስ ሲሆን በሁለተኛው የማጣሪያ ጨዋታ ብቸኛውን ነጥብ ያገኙበትን ፍልሚያ ከታንዛኒያ ጋር 0 ለ 0 በማጠናቀቅ ነበር ማስመዝገብ የቻሉት።


## ትግራይ ክልል

በከሳሽ፡- ከተማ መቐለ ዓ/ሓቂ እና በተከሳሽ፡- ወ/ሮ ሂወት ኣብርሃ ኣባዲ መካከል ባለው የአሰቃቂ ግድያ ሙከራ ክርክር ክስ ጉዳይ እንዲቀርቡ በአድራሻዎ ተፈልገው ስላልተገኙ መከሰስዎን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው በ11/2/2017 ዓ.ም 3፡00 ሰዓት ወደ ከተማ መቐለ ማዕከላይ ፍርድቤት እንዲቀርቡ፤ በተጠቀሰው ሰዓት ካልቀረቡ ግን ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ውሳኔ እንደሚሰጥ የከተማ ማዕከላይ ፍርድቤት አዟል፡፡

**በት/ብ/ክ/መንግሥት መቐለ ከተማ ማዕከላይ ፍርድቤት**

## ኦሮሚያ ክልል

በከሳሽ ወ/ሮ አያንቱ ተስፋዬ እና በተከሳሽ አቶ ሙሉጌታ አበራ መካከል ያለውን የባልና ሚስት ክርክር ጉዳይ በተመለከተ የቡራዩ ክ/ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በ30/1/2017 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠውን ትዕዛዝ በመፈፀም ውጤቱን በቀጠሮ ቀን በ13/2/2017 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት በጽሑፍ ሪፖርት እንዲያደርጉ የቡራዩ ክ/ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**የቡራዩ ክ/ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የቤተሰብ ችሎት ቡድን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

አመልካች ወ/ሮ እቴነሽ እሸቴ ተጠሪ አቶ ለገሰ ግዛው ላይ የመጥፋት ውሳኔ እንዲሰጣቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ካሉ ወይም ያሉበትን የሚያውቅ ሰው ካለ ጥቅምት 25 ቀን 2017 ዓ.ም ጠዋት 4፡30 ሰዓት በአዲስ አበባ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**
**የአራዳ ምድብ ችሎት**

በአመልካች አቶ ከበደ ዋቅጅራ እረና እና በተጠሪ ወ/ሮ ጊዜወርቅ ሰዴታ ሀይሉ መካከል ስላለው የፍ/ብሄር ጉዳይ ተጠሪ ከሐምሌ ወር 2012 ዓ.ም ጀምሮ ከቤት እንደወጡ ሳይመለሱ ቀርተዋል/ጠፍተዋል ስለዚህ ተጠሪ ያሉበትን አድራሻ አውቃለሁ የሚል ካለ በ12/02/2017 ዓ.ም 4፡30 ሰዓት የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉለሌ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማየመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**
**ጉለሌ ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም ዘሀራ ሀሰን አሊዪ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-83431 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር LH113-0124503 ሞዴል KC-LH113V-SRPNS የሞተር ቁጥር 3L-4087228 የሊብሬ ቁጥር 050885 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ4/2/2017 ዓ.ም አመልክተዋል። የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዲስ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

አመልካች፡- ወ/ሮ ሣራ ኃይለማሪያም ታደሰ ተጠሪ፡- አቶ ጌታቸው ግርማ አየለ ተጠሪ ከመስከረም 10 ቀን 1997 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 12 ቀን 2004 ዓ.ም በባህል ልማድ ጋብቻ ተጋብተን አብረን በትዳር ስንኖር ከአብራካችን ያልወለድን ሲሆን ተጠሪ ከነሐሴ 12 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ አብረን ከምንኖርበት አዲስ አበባ ጉለሌ/ክ/ከ/ወ/05 የቤት ቁጥር 147 ከሆነው እንደወጡ ያልተመለሱ ሲሆን በአሁን ሰዓት ተጠሪ የት እንዳሉ አላውቅም። ስለዚህ ተጠሪ አቶ ጌታቸው ግርማ አየለ ያለበትን ወይም አድራሻውን እናውቃለን የሚል ካለ በጉለሌ የአ/አ/ከተማ የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉለሌ ክፍለ ከተማ ምድብ ፍ/ብ/ችሎት 4፡00 ሰዓት ቀርቦ እንዲያስረዳ እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት ጉለሌ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች፡- አቶ ናትናኤል ታደሰ አበበ እና በተከሳሽ/ተጠሪ፡- አቶ አስራት በራሶ ባለ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ኢንሸ 5ኛ ምድብ 5ኛ ንግድ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ20/02/2017 ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ን/ኢ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ ብርትኳን ሽፈራው እና በተከሳሽ ሳሙኤል ላጺሶ መካከል ስላለው የቤት ክስ ጉዳይ ተከሳሽ 14/02/2017ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት አ/አ/ከ የ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለሚኩራ ምድብ 3ኛ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የለሚ ኩራ ም/ችሎት**

አመልካቾች 1ኛ. ወ/ት አዲስዓለም ሽብሩ ወልደገብርኤል በራሴ እና በወኪል አድራጊዎቼ 2ኛ. ወ/ት ፍሬሕይወት ሽብሩ ወልደገብርኤል 3ኛ. አቶ ወንድማገኘ ሽብሩ ወልደገብርኤል ተጠሪ ደመቀች ሽብሩ ወልደገብርኤል አድራሻዋ አይታወቅም፡፡
ተጠሪ ለአመልካቾች እህታችን ስትሆን፣ ይህች እህታችን ከምትኖርበት ከጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 129 ከሆነው ውስጥ እንደወጣች ሳትመለስ ቀርታለች፡፡
ስለዚህ ተጠሪ እህታችን ደመቀች ሽብሩ ወ/ገብርኤል ያለችበትን ወይም አድራሻዋን እናውቃለን የሚል ካለ በ25/2/2017 ዓ.ም አ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉለሌ ክፍለ ከተማ ምድብ ፍ/ብ/ችሎት በ4፡00 ሰዓት ቀርቦ እንዲያስረዳ እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀ/ደረጃ ፍርድ ቤት**
**ጉለሌ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/ሾች ወ/ሮ ራሄል በላቸው በዳኔ እና በተከሳሽ/ሾች አቶ ሀርትል ራልፍ መካከል ስላለው የቤተሰብ ክስ ጉዳይ ተከሳሽ 26/02/2017ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ8፡00 ሰዓት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ/አመልካች፡- መሀመድ ራዲ አብዱልሽኩር እና በተከሳሽ/ተጠሪ፡- ጀማል ሀይደር ሁሴን መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ኢን ምድብ 3ኛ ንግድ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ13/02/2017ዓ.ም በ8፡10 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

አመልካች ወ/ሮ የሺ ሹመት ክፍሌ ተጠሪ አቶ አበራ በዛብህ ላይ የመጥፋት ውሳኔ እንዲሰጣቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ካሉ ወይም ተጠሪ ያሉበትን የሚያውቅ ሰው ካለ ጥቅምት 28/2017 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት አ/አ/ከተማ የ/መ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**
**የአራዳ ምድብ ችሎት**